


ሐ ዋ ር ያ
HAWARYA

ቅጽ 15 | ቁ. 5 | ፋክስ (905)799-2193 | ጥቅምት/ሕዳር 2002
Vol 15 | Issue 5 | Tel (416) 459-5964 | Oct/Nov 2009 | www.hawarya.net | hawarya.publications@sympatico.ca

**መልዕክት**

ክቡራትና ክቡራን አንባቢያን፥ ሐዋርያን በአዲስ መንፈስና ትጋት አስቀጥለናል:: ለጋዜጣችን ሊመጥኑና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሊስተናገዱ የሚችሉ መጣጥፎችንና ሃሳቦችን ትልኩልን ዘንድ በትህትና እናሳስባለን:: የጋዜጣው ድህረ ገጽ በቅርቡ ተሻሽሎ አግልግሎት ይሰጣል::

ከማክበር ሰላምታ ጋር
ከዝግጅት ክፍላችን

# የመስቀል በዓል በድምቀት ተከበረ!

በኢትዮጵያችን በአውራነት ከሚጠቀሱት በዓሎች መካከል አንዱ መስቀል ነው:: ዛሬ ዓለምን በስደት ከሞሉዋት ኢዮጵያዊያን መካከል የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑቱ ወገኖች የመስቀልን በዓል በያሉበት አስበውት ይውላሉ::

መውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የመስቀል በዓል በድምቀት ከሚከብሩባቸው ቦታዎች አንዱ ቶሮንቶ ነው:: በቶሮንቶ ከ40 ሺህ የማያንሱ ኢትዮጵያዊያን ይኖራሉ ተብሎ ሲገመት በከተማዋ ውስጥ ታላላቅ ኢትዮጵያዊያን ተቁዋሞች ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ የኢትዮጵያዊያን ማህበር በታላቁዋ ቶሮንቶና አካባቢው፥ የኢትዮጵያዊ ካናዳዊያን እስላም ማህበረሰብ ማእከል፥ የኢትዮጵያዊያን መረዳጃ እድር ማህበርና ሌሎቹም የተለያዩ ማህበራዊና የሙያ ስብስቦች ሲኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ቀደምትነት ካላቸውና በበቂ እየተደራጁና አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉት መካከል አንዱ ነው::

በከተማዋ ውስጥ በያመቱ የሚከበረው የመስቀል በዓል


ሊሠራ የታቀደው የቤ/ክ ህንጻ ፕላን

የሚዘጋጀው በቶሮንቶ መንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ሲሆን የዚህ ዓመቱ ዝግጅትና ድምቀት እጅግ አስደሳችና አዝ ናኝ ነበር:: በዚህ ደማቅ በዓል ላይ ከሁለት ሺህ በላይ የሚሆኑ የማህበረሰቡ አባላት ሲሳተፉበት የህጻናቱና ታዳጊ ወጣቶች አሸብራቂ ተሳትፎ ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ሰጥቶት ውሉዋል::

በቶሮንቶ የመንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ካቴድራል



በአገልግሎት ላይ ያለ የራሱዋ የሆነ ሰፊ የመሬት ይዞታ ያላት ሲሆን፥ ቅድስትት ካቴድራሉን ኢትዮጵያዊ ይዘቱን እንደተጎናጸፈ በዘመናዊ መልክ ለማነጽ ዝግጅቱ ተፋፍሞ ይገኛል:: በቅርቡ በምእመናኑ ሙሉ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ተመርጦ ሃላፊነቱን የተረከበውና በክቡር አቤል አድማሱ ሊቀመንበርነት የሚመራው ሰበካ ጉባኤ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ሃይልና መንፈሱን አጠናክሮ በዕቅድ ላይ የቆየውን ዘመናዊ የካቴድራል ህንጻ ግንባታ ከግብ ለማድረስ ታጥቆ ተነስቱዋል::

በሰበካ ጉባኤው ሥር ከተዋቀሩት ልዩ ልዩ ንኡስ ኮሚቴዎች መካከለ የህንጻ ግንባታ ኮሚቴ ሲሆን ለዚህ ኮሚቴ ምእመናንና ሰፊው የማህበረሰቡ አባላት በሚችሉት መንገድ ሁሉ ያልተቆጠበ ትብብር እንዲያደርጉ ቤተ ክርስቲያኑዋ ታሳስባለች::

# የካናዳ ብሄራዊ የህዳጣን ህትመትና መገናኛ ምክር ቤት የሊበራሉን ፓርቲ መሪ አስተናገደ!



በሀገር አቀፍ ደረጃ የተደራጀው የካናዳ ብሄራዊ የህዳጣን ህትመትና መገናኛ ምክር ቤት (National Ethnic Press and Media Council of Canada) ለተቃዋሚው የካናዳ ሊበራል ፓርቲ መሪ ለክቡር ማይክል ኢግናቴፍ (Michael Ignatieff) የመደብለ ባህል መገናኛ (multicultural media) መድረክ በማዘጋጀት በልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ገለጻ እንዲሰጥ አደረገ::

ይህ ብዛት ያላቸው ልዩ ልዩ የካናዳ ህዳጣን ማህበረሰቦች የብዙሃን መገናኛ ተወካዮችና እንዲሁም እውቅ የሆኑ የሀገሪቱ መገናኛ አውታሮች የተገኙበት ዝግጅት የተካሄድው ሴፕተምበር 9/2009 (September 09/2009) መሃል ቶሮንቶ ውስጥ በሚገኘው ሃያት ሆቴል (Hyatt Hotel) ውስጥ ሲሆን፥ የክብር እንግዳው የፓርቲያቸውን መርሃ ግብርና በተለያዩ አንኩዋር አንኩዋር ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቋዋም እንዲገልጹ ለተደረገላቸው ጥሪና ዝግጅት አዘጋጁን ምክር ቤት ከልብ አድንቀዋል::

የሊበራሉ ፓርቲ መሪ የፓርቲያቸውን የመሪነት ሥልጣን ከተረከቡ ወዲህ፥ በህዳጣኑ ብሄራዊ የህትመትና መገናኛ ምክር ቤት ተጋብዘው ገለጻ ማድረጋቸው

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ቶሮንቶ ስኮሽያ ባንክ ዋተር ፎል ማራቶን በኢትዮጵያዊያን የበላይነት ተጠናቀቀ፤ በውድድሩ ሦስት ሪኮርድ ተሠበረ



የኢትዮጵያ ሴቶች በአሸናፊነት - ፎቶ በዮሃንስ (የኢትዮጵያ ማህበር)

እሁድ መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በተካሄደው 20ኛው የቶሮንቶ 42 ኪሎ ሜትር ማራቶን ከሴቶች ኢትዮጲያዊያኖቹ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ተከታትለው ገብተዋል::

ኢትዮጵያዊው የአሎፒክ ጀግና ሻምበል ምሩፅ ይፍጠር ባስጀመረው በዚሁ ውድድር፥ አማኒ ጎበና 2 ሰዓት ከ28 ደቂቃ ከ30 ሰኮንድ አዲስ ክብረ ወሰን በማስመዝገብ ቀዳሚ ሆናለች:: የአምናዋ የኦሎምፒክ ሻምፒዮን ሙሉ ሰቦቃ 2 ሰዓት ከ29 ደቂቃ

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

## Hawarya- Amharic Monthly
**Owned by African Network Inc.**

**Muluken Muchie**
Managing Editor/Publisher:

**Mailing Address:**
1116 Wilson Avenue
P.O.Box 66036
Toronto, Ontario
Canada M3M 1G7

Tel:
**416-459-5964**

Fax:
**(905) 799-2193**

E-mail:
hawarya.publications@sympatico.ca

Web Site:
www.hawarya.net

**Graphics & Layout**
Mevlana Media Solutions Inc.
Tel: 416-789-9933
fmelani@rogers.com

Annual Subscription Rate

Canada.... Cdn$35.00

USA....... USD$45.00

Others..... USD$65.00

Institution .... $100. 00
consent of the publisher.


**ለሐዋርያ ደብዳቤና ጽሁፍ ለሚያቀርቡ ሁሉ መመሪያ፤**

1) የሚላኩልን ደብዳቤዎች ከ200 ቃላት ያልበለጡ ቢሆኑ ይመረጣል:: (አጫጭርና ፍሬ ነገሮችን ጨምቀው የሚያቀርቡልን ደብዳቤዎች የበለጠ የመታተም እድል ይኖራቸዋል)
2) ጥናታዊና ትምህርታዊ ሰፋፊ ጽሁፎች፡-
ሀ) በኮምፒተር የአማርኛ ጽሁፍ ማቀናበሪያ የተዘጋጁ ከሆኑ ከ3 ገፆች፥
ለ) በእጅ ጽሁፍ ከቀረቡ ከ5-7 ገፆች ባይበልጡ ይመረጣል፤ ወቅታዊነት ያላቸው፥ ትምህርታዊ የሆኑ፥
ያልተዛዙ ... ጽሁፎች ቀድመው የመታተም እድል ይኖራቸዋል::)
3) ማንኛውም ደብዳቤም ይሁን ጥናታዊና ትምህርታዊ ጽሁፍ አቅራቢ ስሙን፥ አድራሻውንና ስልክ ቁጥሩን አብሮ መላክ ሲኖርበት፥ ከዝግጅት ክፍሉ ጋር የሚደረጉ የግንኙነት መረጃዎች በሚስጥር ይያዛሉ::
4) ለሐዋርያ የሚላኩ ጽሁፎች ሁሉ የጋዜጣው ንብረት ሲሆኑ ይዘታሰውንና መጠናቸውን ተገቢ ለማድረግ የአዘጋጆች የማስተካሾል መብት የተጠበቀ ነው::
5) በኢዲቶሪያል አምዱና የዝግጅት ክፍሉ ከሚያቀርባሰው ዝግጅቶች ውጭ፥ በዚህ ጋዜጣ ለሚቀርብ ማንኛውም ጽሁፍ ይዘት አዘጋጁና አሳታሚው ሃላፊነት አይወስዱም::

# የኒው ዮርክ ቤተ መጽሐፍ ማህበር ዓመታዊ የ ንግድ ትዕይንትና ኮንፈረንስ አካሄደ፤



በአሜሪካ ደረጃ በስፋታቸውና በረጅም ዘመን ማህበራዊ አገልግሎታቸው ከሚታወቁት ታላላቅ ተቋዋሞች መካከል የኒው ዮርክ ቤተ መጽሐፍ ማህበር (New York Library Association - NYLA) አንዱ ነው:: ይህ ማህበር የተመሠረተው በ1890 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ሲሆን በያመቱ ሰፊ የ ንግድ ትዕይንትና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የሚወያይ የክብ ጠረጴዛ ኮንፈረንስ ያካሂዳል:: ከሚያካሂዳቸው ዓመታዊ ኮንፈረንሶች መካከል ማህበራዊ ሃላፊነትን በተመለከተ የተዘጋጀ ክብ ጠረጴዛ ውይይት፥ የመጽሃፍ ቤት አገልግሎት፥ የምሁራን ነጻነት፥ የመንግሥት ዜና መረጃና ሌሎች በዛ ያሉ ክብ ጠረጴዛ የውይይት ኮንፈረንሶች ይገኙበታል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአቻነት መድረክ የተሰጠውና እንደሌሎች የክብ ጠረጴዛ ውይይት ኮንፈረንሶች የጊዜ ሰንጠረዥ ተሰጥቶት የሚካሄደው መድበለ-ማህበራዊ የብዙሃን ህትመት ውጤቶች (multicultural – ethnic - press) የተባለው ፕሮግራም ነው::

የዚህ ዓመቱ 2009 ዓመታዊ የ ንግድ ትእይንትና የክብ ጤረጴዛ ኮንፈረንስ ከኦክቶበር 14-17/2009 (እ.ኤ.አ) በኒው ዮርክ ግዛት ኒያጋራ ፎል (Niagara Fall, NY) ውስጥ ተካሂዷል:: በዚህ ኮንፈረንስ ለመድበለ ማህበራዊ የብዙሃን ህትመት ውጤቶች (multicultural – ethnic- press) ክብ ጠረጴዛ ውይይት ተሳታፊዎች ገለጻ እንዲያደርጉ ከደቡብ ኤሺያ፥ ከአውሮፓና አፍሪካ ሦስት ማህበራዊ የብዙሃን መገናኛዎች የተጋበዙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ጋዜጣችን ሐዋርያ ለመልካሙ እድል ተቋዳሽ ነበር::

ሐዋርያን በመወከል የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ አቶ ሙሉቀን ሙጨ በግብዣው መሠረት በሠዓቱና በቦታው ተገኝቶ ኮንፈረንሱ ባስያዘው የመወያያ ርእስ ላይ የበኩሉን መንደርደሪያ ንግግር በማድረግ ተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት እንዲያካሂዱበት አስተዋፅኦ አድርጓል:: ለዚህ ክብ ጠረጴዛ ውይይት ተይዘው የነበሩ የውይይት ርእሶች ሁለት ሲሆኑ እነሱም የመድበለ ማህበራዊ የህትመት ውጤቶች የሚያገለግሉት ማህበረሰብ በአዲስ አገርና ባህል ውስጥ ተለማምዶ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ሐዋርያ ትቀጥል!

## ሰላምታየ ይድረሳችሁ

ቆየት ያልኩ የጋዜጣችሁ አንባቢ ነበርኩ:: እንደዛሬው የዜና ማግኛው መስኮት ሳይበዛ ሐዋርያ በወቅቱ ያበረከተችው አስተዋፅኦ ወደር አይገኝለትም ከሚሉት አንዱ ነኝ:: ዛሬ ላይም ቢሆን የማይናቅ አስተዋፅኦ ልታደርግ እንደምትችል ቢገመትም ልክ እንደ አገር ቤቱ የነፃው ፕሬስ አቻዎቿ ድምጿ ሰለለብን:: ባገር ቤት ይታተሙ የነበሩ ህትመቶች ድምጽ መጥፋት ምክንያቱ ግልጽ ቢሆንም የሐዋርያ ግን አስገራሚ ሆኖብናል:: በተለይም የበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው ሐዋርያ የሀገራችን ፖለቲካ ልብ ጠልቃ እንደምታውቅ እየታወቀ የደፈረሰውን ለማጥራት እጅግ በምትፈለግበት ወቅት ብቅ እልም ማልትዋ ነው::

እባካችሁ ን ቀጥሉ:: ኢንተርኔትና ፓልቶክ የተስፋፋበት ጊዘ ቢሆንም በቋንቋችን የሚዘጋጁ የህትመት ውጤቶች ያስፈልጉናልና ልትበረቱና ተወዳጁን አገልግሎታችሁን ልትቀጥሉ ይገባል፡ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ማለቱን አቁማችሁ የተለመደውን አገልግሎታችሁን ቀጥሉበት:: ይህቺን ደብዳቤ የጻፍኩላችሁ አሁን ሐዋርያ ተከታትላ መውጣት ስለጀመረች ላበረታታችሁ ፈልጌ ነው:: ግፉበት ከጎናችሁ ነን::

አድናቂያችሁ
ዘመዴ

ሐዋርያ፡ ውድ ዘመዴ፥ ሰላምታችንን እናስቀድማለን:: የማይጠገብ መልእክትዎን ተመለከትን:: እንደብዙዎች የሐዋርያ ወዳጆች የጋዜጣችን አረማመድ ያሳሰብዎት መሆኑን እንረዳለን:: ስለ ሀገራችን ፖለቲካ ባነሱት ጉዳይ ላይ ብዙ ማለት ቢቻልም ለጊዜው በአርምሞ እንለፈው:: ስለ ኢንተርኔት ግኝትና ውጤቶቹ ስለሆኑት (ምሳሌ፥ ዘመነኛው ፓልቶክ) ግን ትንሽ እንጨዋወት:: እነዚህ በዘመናችን ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የብዙሃን መገናኛ አውታሮች ጠቀሜታቸው ሰፊ መሆኑ አይካድም:: ነገር ግን በማንኛውም መስፍርት ነባሮቹን የብዙሃን መገናኛዎች ተክተውና እራሳቸውን ችለው ይቆማሉ የሚል ግምት ወይም ጥርጣሬ እንዳይኖረን ግን ማስገንዘብ እንሻለን:: ኢንተርኔት ነባር የብዙሃን መገናኛዎችን ተግባር ለማፋጠንና ለማስፋፋት ይጠቅም እንደሆን እንጅ ራሱን ችሎ ቁዋሚና ታማኒነት ያለው ተቋም አይደለም:: ኢንተርኔት ዓለምን በኪስ ይዞ የመጓዝ ን ያህል ቢቆጠርም፥ ከመገናኛ ብዙሃን አንጻር፥ እስካሁን የሚታወቁትን ታማኝ የብዙሃን መገናኛ ወጤቶችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰፋ ላለ ያንባቢ ክፍል አቀረበልን እንጅ የፈጠረልን ልዩ መረጃ የለም:: በሚገባ የተብላላና ታማኝነት ያለው ዜና ለማግኘት የሙያው ባለቤት የሆኑና በህገ ደንብ የሚተዳደሩ የዜና አውታሮች ያስፈልጋሉ:: ለምሳሌ፥ ሐዋርያ ከሌለች በጋዜጣዋ አቅም ፈልፍላ የምታገኛቸው መረጃዎች ኢንተርኔት ዉስጥ በቀላሉ አይገኙም:: ግለሰቦች ከዚህም ከዚያም በተለያየ መንገድ ዜናዎችን በኢንተርኔት ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ነገር ግን አስተማማኝነቱና ተጠያቂነታቸው ጥያቄ ውስጥ የገባ ነው:: የዘመናችን እጹብ ድንቅ የቴክኖሎጅ እድገት እጅግ ያነሰ የሰው ሃይል ቢጠይቅም ያለሰው ልጅ ቅንብር ወይም ድጋፍ ዋጋ እንደለለው ሁሉ፥ የኢንተርኔት የብዙሃን መገናኛነትም እንበለ ታማኝና ሙያተኛ አቅራቢ ብላሽ ነው:: እናም፥ የድህረ ገጹ (ኢንተርኔት) ግዝፈት የሐዋርያንና መሰል የብዙሃን መገናኛዎችን ሊሸፍን አይችልም፤ ቢያግዛቸውና ቢያቀላጥፋቸው እንጅ::

ለማንኛውም ግን፥ እንደታዘቡት ሁሉ ሐዋርያ ተጠናክራ መቀጠሉዋን ልናረጋግጥልዎ እንሻለን:: ወጣ ገባውን አልፈን ደልዳላው መንገድ ላይ የደረስን ይመስለናል:: ድጋፋችሁ አይለየን፥ ዛሬም እንደድሮው መጣጥፎችንና አስፈላጊ ጥቆማዎችን ላኩልን::

ከምስጋና ጋር
ከአዘጋጁ

# የወያኔ የተለመደ ቅጥፈትና ማደናገሪያ

## ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም. (October 15, 2009 )

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ክለላ መስከረም 29 ቀን 2002 ዓ.ም. (October 9, 2009) እንደሚጀመር በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተመው ዕለታዊ የሱዳን ጋዜጣ ሱዳን ትሪቢውን መስከረም 8 ቀን 2002 ዓ.ም. ( September 18, 2009 ) ከዘገበው በኋላ፤ የድንበር ኮሚቴው ጉዳዩን በተመለከት ለኢትዮጵያውያን ወገኖቹ መስከረም 16 ቀን 2002 (September 26, 2009) ዓ. ም. መግለጫ ማውጣቱ የሚታወስ ነው። ከዚያም በማስከተል፤ የድንበር ኮሚቴው አባላት ለልዩ ልዩ የዜና ማሰራጫ አውታሮች በሰጡት ቃለ-ምልልሶች ወያኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የሚሸርበውን ሥውር ደባ አጋልጠዋል። አሁንም በማጋለጥ ላይ ይገኛሉ።

ይህ ከፍተኛ የሃገር ክህደት ሊቀሰቅስ የሚችለውን ኢትዮጵያዊ ቁጣና ከዚያም ተከትሎ የሚመጣውን አደጋ በመገንዘብ፤ የወያኔ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በድረ-ገጹ ላይ ወደ መስከረም 2002 ዓ.ም. መጨረሻ አንድ ማደናገሪያ መግለጫ አውጥቷል። ይኸው ማደናገሪያው መግለጫ በአጭሩ እንዲህ ይላል፡-

“ አርብ መስከረም 18 ቀን 2009 በሱዳን ትሪቢውን ድረ-ገጽ ላይ በሱዳንና በኢትዮጵያ የድንበር ክለላው በጥቅምት 9 ቀን 2009 ይጀመራል ብሎ የሱዳንን የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር በመጥቀስ ያወጣው ዜና ስህተት እና የሱዳንና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኮሚቴ (Ethio-Sudan Political Committee) ከግንቦት 18 እስከ 19 ቀን 2009 በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ስብሰባ አድርጎ ያስተላለፈውን ውሳኔ የሚቃረን ነው። በውሳኔው መሰረት፤ የፖለቲካው ኮሚቴ ለጋራ ድንበር ኮሚቴው (Joint Boundary Committee) የሰጠው ትእዛዝ ጠቅላላ ድንበሩን በአስቸኳይ ከዜሮ ነጥብ ወደ ደቡብ አቅጣጫ የሚያጠቃልል ሙሉ በሙሉ ቅየሳና ቅኝት (Survey and reconnaissance) የሚደረግበትን የጊዜ ሰንጠረዥ እንዲያዘጋጅ ነው።የፖለቲካው ኮሚቴ ሌላው የተስማማበት ደግሞ፤ የአጠቃላይ የድንበሩ ቅየሳና ቅኝት ከማለቁ በፊት ዳግም የድንበር ክለላ (re-demarcation )እንደማይጀመር ነው።በጋራ ፖለቲካ ኮሚቴ ውሳኔ አኳያ፤ የጋራ ድንበር ቴክኒክ ኮሚቴ አዲስ አበባ ላይ ግንቦት 20 ቀን 2009 ባካሄደው ልዩ ስብሰባ የተስማማው፤ አጠቃላይ የድንበሩ ቅየሳና ቅኝት በጥቅምት 15 ቀን 2009 ተጀምሮ እስከ ግንቦት 2010 መጠናቀቅ እንዳለበት ነው። በዚሁ መሠረት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በራሱ በኩል በአለው የጋራ ድንበር ቴክኒክ ኮሚቴ የታቀደ ቅየሳና ቅኝት ሥራን ለማካሄድ የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት በማካሄድ ላይ ነው። የሱዳን ሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ድንበር ክለላው በሚቀጥለው ወር ይጀመራል ብለው የሰጡት መግለጫ ስህተት ነው። ስህተቱም ከቅንነት የመነጨ ነው ብለን እናምናለን...” ይላል።

እንደተለመደው የወያኔ ቡድን ቃሉን ከማጠፉ በፊት፤ ይህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ መግለጫ ያመናቸውን ሦስት ( 3 ) አብይ ጉዳዮች ማገናዘብ ተገቢ ነው። እነርሱም፡-

1ኛ. የኢትዮጵያና ሱዳን የፖለቲካ ኮሚቴ (Ethio-Sudan Political Committee) ተብሎ የሚጠራ ከፍተኛ አካል መኖሩና የኢትዮጵያና የሱዳን የጋራ ድንበር ኮሚቴም (Ethio-Sudan Joint Boundary Committee) በፖለቲካው ኮሚቴ ሥር እንደሚሠራ፤

ይህ የኮሚቴ አወቃቀርና አሰራር ለረጅም ዓመታት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተደብቆ የቆየና ወያኔ ሲጋለጥ ተጨንቆ ያወጣው ምስጢር ነው።

2ኛ. የኢትዮጵያና የሱዳን የጋራ የድንበር ኮሚቴም (Ethio-Sudan Joint Boundary Committee) ከጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም. (October 15, 2009) እስከ ግንቦት 2002 ዓ.ም.(May 2010) ድረስ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበርንና አካባቢውን ሙሉ በሙሉ እንደሚቀይስና ቅኝት እንደሚያደርግ፤

ይህ ደግሞ ወያኔ ሲጋለጥ ያወጣው ሌላው ምስጢር መሆኑና እንዲያውም ሱዳን ትሪቢውን ያወጣውን ዜና የሚያጎለምስና የሱዳን ሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ድንበሩን ለማካለል የሚያደርገውን ዝግጅት የሚያስተጋባ ነው። 2

3ኛ. የድንበር ክለላው ከግንቦት 2002 ዓ.ም. ( May 2010) በኋላ እንደሚደረግና ከዚህም ጋር አያይዞ ወያኔ ያለፉት የኢትዮጵያ መንግሥታት የተቀበሉት የድንበር ክልል እንዳለ አስምስሎ በማቅረብ አሁን እርሱ የሚያካሂደው ዳግም የድንበር ክለላ ( re-demarcation ) እንደሆነ መግለጹ፤

ወያኔ ያለፉት የኢትዮጵያ መንግሥታት የተቀበሉት የድንበር ክልል የሚለው ደግሞ፤ ሜጀር ( ሻለቃ ) ጉዊን የተባለ የእንግሊዝ ጦር መኮንን በ1902 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) አስምሬአለሁ የሚለውን የወሰን ክልል ነው። ይሁንና የእንግሊዝ ቅኝ ገዥ ሻለቃ ያሰመረው መስመር መሠረት በማድረግ ፀረ-ኢትዮጵያ ወያኔ ቡድን ለሱዳን ይገባታል ብሎ ሽንጡን ገትሮ ኢትዮጵያን የሚሟገትበት የመከራከሪያ ነጥብና ቅጥፈት የሚከተሉት ታሪካዊ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደርጉታል፡-

1.ሻለቃ ጉዊን መሬቱን አካልያለሁ ሲልና በወረቀት ሲያሰምር፤ በኢትዮጵያ በኩል አንድም ተወካይ ስለአልነበረ የጉዊን የድንበር ማካለል ተግባር ከቅኝ ገዢዎች ማንአለብኝነት ተለይቶ ስለማይታይና የውል አፈጻጸም ሥርዓት የማይከተል በመሆኑ፤

2.የ1896 ዓ.ም.(እ.አ.አ.) አድዋ ጦርነት ድል በቅኝ ገዥዎች ላይ በፈጠረው ከፍተኛ መደናገጥ ምክንያት 1902 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) አካባቢ እንግሊዝና ጣሊያን በጋራ በመመሳጠር የሰሜንና የምዕራብ ኢትዮጵያን ድንበር ለመግፋት የማይፈጽሙት ሴራ ስለአልነበርና የሻለቃ ጉዊን ተልዕኮም ከዚያ ተገንጥሎ ሊታይ ስለማይችል፤

3.ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በፊትም ይሁን በኋላ ይህ ሻለቃ ጉዊን ከለለው የሚባለው መሬት ምን ጊዜም ከኢትዮጵያ ይዞታ ውጭ ሆኖ ስለማያውቅ፤ እንዲያውም በአፄ ቴዎድሮስና በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት አሁን ሱዳን ተብሎ ከሚጠራው ሃገር በጣም ወደ ውስጥ የገባ ስለነበር፤ አሁን የመሬት ጥያቄ ከተነሳ የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ ታሪካዊ መሠረት የአላት ኢትዮጵያ በመሆኗ፤

4.አሁን ወያኔ ለሱዳን ለመስጠት የሚደገስበት የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሰፊ ውሃ-ገብ ለም መሬት ደግሞ ለብዙ መቶ ዓመታት በኢትዮጵያ ድንበር ጠባቂዎችና የጎበዝ አለቆች እንደ ዓይን ብሌን እየተጠበቀ ለመቆየቱና ዕልፍ አዕላፍ ውድ ሕይወት እንደተከፈለበት ሕያው የታሪክ ማስረጃዎችና የሚታዩ ሰብዓዊና ተፈጥሯዊ ምስክሮች ስለሚገኙ፤

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ማስረጃዎችና በዓለም-አቀፍ የአሠራር ደንብ መሠረት፤ ወያኔ ከሱዳን ጋር የሚያደርገው የድንበር ክለላ ስምምነት ውድቅ ነው። ከዚህም ባሻገር፤ ከዋናው ባለጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በስተጀርባ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ስምምነት ይሁን የድንበር ክለላ ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ፈንጂ እንጂ ምንም ዓይነት ተቀባይነት እንደማይኖረው መታወቅ አለበት።

ከዚህም ሌላ ወያኔ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ብሎም ለማፈራረስ የተጠቀመበተ ዘዴ የቅኝ ገዢዎች ለራሳቸው ጥቅም ማስጠበቂያ ያሰመሩትን የድንበር መስመር በመቀበልና የቅኝ ገዢ ጠበብትን እንደ ምስክር በመጠቀም ነው።

ይህ የወያኔ ገዢ ቡድን ሃገራችን ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ለማጥፋት የሚያደርገውን የረቀቀ ውስብስብ ደባና ተንኮል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በጽሞና ተረድቶ፤ በልቡ ቀርጾ ይዞ ለታሪክና ለትውልድ ማስተላለፍ አለበት። ምን ያህል ወደር የሌለው ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ስሜት በወያኔ ደም ሥር ውስጥ እንዳለ ለማስረዳት፤ የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ለወያኔ ፓርላማ ማክሰኞ ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. የኢትዮጵያንና ሱዳንን ድንበር ጉዳይ በተመለከተ ባደረገው ንግግር የሱዳን ሕዝብና መንግሥት ብሔራዊ ጥቅም አስጠባቂና ተሟጋች ጠበቃ በመሆን የተናገረውን እንጠቅሳለን፡-

“የእኔ የኔ ነው የእናንተን እንካፈል የሚል የኢትዮጵያን ተስፋፊነት አቋም ተሸክሞ ነው ያደረው፤ ይህን ተቀብሎ ነው ያደረው የሱዳን መንግሥት፣ ይህን ተቀብሎ ማደሩ ደግሞ እንደ ጅልነት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፤ አርቆ አሳቢነትን ያመለክታል፣ የጋራ ጥቅም ማየትን ያመለክታል።” 3

ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ!

የአንድ ትውልድ ኃላፊነት ቀዳማይ ትውልዶች ያስተላለፉትን የሃገርን ድንበርና ቅርስ፣ ቢቻል አሻሽሎና የበለጠ አጠናክሮ ባይቻል ደግሞ የተረከበውን ሙሉ በሙሉ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ነው።

አሁን በሕይወት ያለው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ከአባቶቹ የተረከባትን ኢትዮጵያ ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት። እነ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ፣ ራስ አሉላ አባ ነጋ፣ አፄ ምኒልክ፣ ቀስቶ፣ አባ ጅፋር፣ ደጃዝማች ዑመር ሰመተር፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ደጃዝማች አበረ ይማም፣ ቢትወደድ አሊ ሚራህ፣ ራስ ውብነህ ተሰማ፣ ቢትወደድ አዳነ መኮንን፣ ሻለቃ አጣናው ዋሴ፣ ከዚያም የኡጋዴን፣ የቦረና፣ የገለብና ሃመርባኮ፣ የጋምቤላ ጀግኖች፣ ከዚያም ተያይዞ በቤንሻንጉል፣ በአሶሳ፣ በአሜድላ፣ በቋራ፣ በአርማጭሆ፣ በጠገዴና ወልቃይት የኖሩ አያሌ ገበሬና ከብት አርቢ ወገኖቻችን፤ የኢትዮጵያን ድንበር ያስተላለፉልን በተለያዩ ጊዜያት የመጡትን ወራሪዎች ጋር በመፋለም ታላቅ ታሪካዊ ጀግንነት በመስራት በአጥንታቸው አጥረውና በደማቸው አስምረው ነው።

እነዚህ አባቶቻችንና እናቶቻችን ያን ያደረጉት ፣ ቤተሰቦቻቸውን ተሰናብተው ደረቅ ስንቅ ጭነው ለብዙ ወራት በባዶ እግራቸው ተጉዘው አስፈሪ በርሃና ዱር ወንዝና ኸረት አቋርጠው፤ ብዙዎችም በውሀ ጥም፣ በርሃብና በበሽታ መንገድ ላይ ቀርተው የተረፉት ድንበሩ ደርሰው በጦርና በሠይፍ ውርጅብኝ መካከል አልፈው ሕይወታቸውን ሰጥተውበት ነው። በተጨማሪም የታሪክ ማኅደር እንደሚያስረዳን፤ አሁን ወያኔ ለሱዳን ለማስረከብ የሚደግስለት የመተማ አካባቢ መሬት አፄ ዮሐንስ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ከወራሪው የሱዳን ደርቡሽ ጦር ጋር በመፋለም አንገታቸውን በሰጡበት በመጋቢት 2 ቀን 1881ዓ.ም. ዕለት ከትግራይ፣ ከጎንደር፣ ከወሎና ከሌሎች ቦታዎች ለብዙ ወራት ተጉዘው በቦታው የተገኙ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ታሪካዊ ጀብዱ ፈጽመው ለሃገራቸው ክብር ደማቸውን ያፈሰሱበትና አጥንታቸውን የከሰከሱበት ቦታ ነው።

ታዲያ ስንት መስዋዕትነት የተከፈለበትን ሃገር የውያኔ ቡድን አያት ቅድመ-አያቶቻችን በሠሩት ቤተ መንግሥት መሽጎ የሃገራችንን ዳር ድንበር እንደ ዳቦ እየቆረሰ ለባእድ አገር በችርቻሮ ሲያስረክብ ዝም ብሎ እንደማየት የበለጠ አስነዋሪና አሳፋሪ ሕይወት ሊኖር አይችልም። ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህን የሃገር ክህደት እጥብቆ ሊቃወመውና ሃገራዊ ግዴታውን ለመወጣት የሃገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር ቆርጦ መነሳት አለበት።

ስለዚህ በወቅቱ ከእየአንዳንዳችን የሚጠበቀው ከዋናው ባለጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በስተጀርባ፤ የድንበር ጠባቂ ወገኖቻችንን በማፈናቀል እየተደረገ ያለውን የሃገር ክህደትና የመሬት ችርቻሮ ለድንበሩ ቀናኢና ለወገኑ ተቆርቋሪ ለሆነው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ማለትም፡- ለወታደሩ፣ ለአርሶ-አደሩ፣ ለወዝ-አደሩ፣ ለመንግሥት ሠራተኛው፣ በተለያየ የሥራ ዘርፎች ለተሰማራው ሙያተኛ፣ ለተማሪው፣ ለወጣቱ፣ ለሴቶችና አረጋውያን በያሉበት ዜናዎችን በአፋጣኝ በማድረስ በአንድነት እንዲነሱና አቅማቸው በፈቀደው ደረጃ ሃገር ከሃዲውንና ሻጭ የወያኔ ቡድንን በአጽንዖት እንዲታገሉና እንዲቃወሙ ጥሪ ማቅረብ ነው።

የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በቆራጥ ልጆቿ ተጋድሎ ይከበራል!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ

# አረንጓዴው ጎርፍ በቶሮንቶ



ምሽቱን ሲዘንብ በማደሩ ይመስላል ንጋቱ ቀዝቃዛማ÷ መሬቱም በውሃ የራሰ ነበር:: በዓመት አንድ ጊዜ የሚደረግና ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ አትሌቶች የሚሳተፉበት የውድድር ቀን ነው:: ፉክክሩን ለመመልከትና በዚህ ታላቅ ውድድር ላይ የሚሳተፉትን ስፖርተኞች ሞራል ለመስጠት የቶሮንቶ ኑዋሪዎች የአየሩ ጸባይ ሳይበግራቸው ከውድድሩ መጀመር አስቀድመው ከመወዳደሪያው ሥፍራ ተገኝተዋል:: በዚህ ውድድር ከ40 ሀገራት የተጋበዙ አትሌቶችን ጨምሮ 20 ሺህ ሰዎች ለመሳተፍ ተመዝግበው መነሻ ሰዓት በመጠባበቅ ላይ ናቸው:: የዱከም ሬስቶራንት ባለቤት ማይክ ቅዱስ ባዘጋጀልን የመግቢያ ፈቃድ ወደ ውድድሩ መጀመሪያ ስፍራ ዘለቅን:: ይህን ዘገባ ለሐዋርያ ጋዜጣ ለማቅረብ በነበረኝ ጥረት ከተመደበልኝ ስፍራ ቆሜ ግራ ቀኙን አማተር ያዝኩኝ:: በውድድሩ ለመሳተፍ ከኢትዮጵያ የመጡትን የኢትዮጵያ ቡድን አባላት ከመወዳደሪያው ስፍራ አየሁዋቸው:: ሁሉም ማለት ይቻላል አዲስ ናቸው:: ውድድሩን ለመመልከት ወይም ለመዘገብ የመጡትን መቃኘት ያዝኩ:: በቅርብ ርቀት ጀግናው ሻምበል ምሩጽን አየሁት:: ወዳለበት አመራሁና ሰላምታ አቀረብኩ:: አጸፋውን በአክብሮት መለሰልኝ:: “ባንዴራ አልያዝክም?” አለኝ:: በተለይ ከአገር ርቆ ለሚኖርና ለሚወዳደር ባንዴራ ትልቅ ትርጉም አለው:: በግሌ አፈርኩ፤ ምመልሰው አጣሁ:: ወዲያው ውድድሩ ሊጀመር ጥቂት ሰኮንዶች ስለቀሩት የውድድሩ አስጀማሪ ኢትዮጵያዊውን ጀግና ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር ወደ ማስጀመሪያው ስፍራ እንዲመጣ “ይፈለጋሉ” የሚል መልእክት ተላለፈ:: አይኖቹ በእንባ ተሞሉ:: የውድድሩን አዘጋጆች በልቤ ደጋግሜ አመሰገንኩዋቸው – ኢትዮጵያዊውን ጀግና ባለመርሳታቸውና በማክበራቸው::

ሻምበል ምሩጽ ውድድሩን አስጀመረ:: አረንጓዴው ጎርፍ በቶሮንቶ ጎዳናዎች ላይ ፈሰሰ:: ይህ ጎርፍ የዛሬ 30 ዓመት ገደማ በአይነ ህሊናዩ ተመለስኩ፤ እ.ኤ.አ 1980 የተካሄደው የሞስኮ ኦሎምፒክ::የዚያን ጊዜ ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር እና ጓደኞቹ እርስ በርስ በመረዳዳት ባደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ የሞስኮን ኦሎምፒክ ስተዲዬም ያጥለቀለቁት ውድድር ታወሰኝ:: እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ያለማቋረጥ በትውልድ ቅብብሎሽ አረንጓዴው ጎርፍ በአውሮፓ÷ አሜሪካ÷ ኤሽያና አፍሪካ ከተሞች በመፍሰስ ላይ ነው:: ጀግና ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች የኢትዮጵያን ባንዴራ ከሁሉም ልቃ እንድትውለበለብ÷ መዝሙሯም እንዲዜምና እንዲሰማ÷ መገናኛ ብዙሃንም የኢትዮጵያዊያንን ጀግንነት እንዲዘግቡ በማድረግ ላይ ነው:: ይህንን እያሰላሰልኩ እንዳለሁ የማራቶን ሯጮች አስር ኪሎ ሜትር ማጠናቀቃቸውንና በወንዶችና በሴቶች ኢትዮጵያዊያኑ እየመሩ መሆኑን የውድድሩ አዘጋጆች በፊልም አስደግፌው ሰበር ዜና አሰሙን:: በስፍራው የነበረው ስፖርት አፍቃሪ በጭብጨባ አካባቢውን አደመቀው:: ውድድሩ ቀጥሏል:: የአብዛኛው ተመልካች አይን ከውድድሩ መድረሻ ሮስቅራቢያ ከተሰቀለው ትልቅ የቴሌቪዥን ስክሪን ላይ አልተነቀለም:: የማራቶን ሯጮች 21 ኪ/ሜትሩን ማጠናቀቃቸውንና አሁንም ኢትዮጵያዊያኑ እየመሩ መሆኑን ከተነገረ በተወሰኑ ደቂቃዎች በሁዋላ የግማሽ ማራቶን ሯጭ በውድድሩ ማጠናቀቂያ ስፍራ ደረሰ÷፤ ኬኒያዊው ኬንዝ ሙንጋራ ነበር:: እሱ ከገባከአንድ ሰዓት በሁዋላ ተወዳዳሪዎቹ መግባታቸውን አላቋረጣጡም::

በዚህ ውድድር ላይ “ስፖርት ለጤንነት” በሚል መርህ አዛውንቶች÷ ጎልማሶች÷ ወጣቶች– በአጠቃላላው ከሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች÷ የአካል ጉዳት ያለባቸው ደግሞ በዊልቸር ተሳትፈዋል:: አንዳንዶች ከውሾቻቸው ጋር ሩጠዋል:: የውድድሩ አስተባባሪዎች÷ የማራቶን አትሌቶች 30ኛ ኪ/ሜትር ማጠናቀቃቸውን አብስሮ ውድድሩን እየመሩ ያሉት እንዲሁ ኢትዮጵያኑ መሆናቸውን አክለው::

የማራቶን ውድድር ጠንከር የሚለው ከ30ኛው ኪ/ሜትር በሁዋላ ነው ይባላል:: የበርካታ ድሎች ባለቤት የሆነው ጀግናው ሻለቃ ሃይሌ ገብረ ሥላሴ በቅርቡ በርሊን ማራቶን ካጠናቀቀ በሁዋላ እንዳለው እስከ 35ኛው ኪ/ሜትር ድረስ በራሱ የተያዘውን የማራቶን ሪኮርድ ለመስበር ከሁለት ሰዓት በታች ለመግባት ሰዓቱን በአግባቡ እየተቆጣጠረ በመወዳደር ላይ እንደነበረ ነገር ግን ከ35ኛው ኪ/ሜትር በሁዋላ ድካም እንደተሰማው ገልጿል:: ውድድሩን በቀዳሚነት ጨርሶ ሪከርዱን ለመስበር ለጊዜው ባይታደልም ሃይሌ በወቅቱ ለጋዜጠኞች እንደተናገረው ማራቶን የሚከብደው ከ35ኛው ኪ/ሜትር በሁዋላ ነው ብሏል:: ለዚህም ይመስላል በአጀብ ይጓዙ የነበሩት የቶሮንቶ ዋተር ፍል ማራቶን ሯጮች ይኸው ከላይ የተነሳው የሃይሌ ገጠመኝ ተገጣጥሞባቸው ሳይሆን አይቀርም ውድድሩን ይመሩ የነበሩት በቅርብ ርቀት ለሚከተሏቸው መሪነቱን አስረከቡ:: ጫላና ጋሻው ለኬኒያዊው ኬንዝ ሙንጋራ÷ ሙሉ ሰቦቃ ደግሞ ለአማኒ ጎበና መሪነቱን አስተላለፉ:: በዕለቱ የነበረውን ነፋሻማ እምቅ እየር ተቋቁመው አትሌቶቹ ከውድድር ማጠናቀቂያው ስፍራ ሲደርሱ በአካባቢው የነበረው ሕዝብ በከፍተኛ ሞራልና ጭብጨባ ተቀበላቸው:: ከዚህ በፊት የተያዘውን ሪከርድ ለመስበር በመቃረባቸው ሕዝቡ ከፍተኛ ሞራል ይሰጣቸው ነበር:: ሞራሉ ብርታት ሆኗቸው ይመስላል ፍጥነት ጨምረው ኬኒያዊው ኬንዝ ሙንጋራ እና ኢትዮጵያዊው ጫላ ለሚ ተከታትለው በመግባት የስፍራውን ሪኮርድ ሰበሩ::

የወንዶች የማራቶን ተሳታፊዎች በመግባት ላይ ናቸው:: በስፍራው የተገኘው የስፖርት አፍቃሪ ድጋፍ እየሰጠ ሳለ የሴት የማራቶን ሯጮች ከውድድር ማጠናቀቂያው ስፍራ መቃረባቸው ተነገረ:: ጭብጨባው ቀጠለ:: በድንገት አንድ ሰው 21 ኪሎሜትሩን 42 ኪሎ ሜትር ከሮጠችው ከኢትዮጵያዊቷ አትሌት ከማኒ ጎበና ጋር በእኩል ሰዓት ውድድሩን ጨረሰ:: በስፍራው የነበርው ሰው ከፍተኛ ሞራል ሰጠው:: የጋዜጠኞች ትኩረትም ወደዚህ ሰው ዞረ:: በዚህ ውድድር ከመሳተፉ በተጨማሪ በመጭው ምርጫ እንደማይሳተፍ በመግለጹ ነበር ከንቲባ ዴቪድ ሚለር ትኩረት የሳበው:: በዚህ መሃል አትሌት አማኒ ጎበና ረከርድ በመሥበር ሩጫዋን ማጠናቀቋ ከፍተኛ አድናቆት ነበር ከተመልካቹ የተቸራት:: ከዚያም የአምናዋ ሻምፒዮን ሙሉ ሰቦቃና ከበቡሽ ሃይሌ ተከታትለው በመግባት በአካባቢው የነበረውን የሥፖርት እፍቃሪ አጀብ አሰኙት:: ባንዴራችን ከፍ ብላ እንድትውለበለብና የሀገራችን ስም በማስጠራታቸው ምስጋና ይግባቸው:: እነዚህ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በቶሮንቶ ጎዳናዎች ላይ ስለ መተባበር÷ በአንድነት ለአንድ ዓላማ መሥራት ምን ያህል ውጤታማ እንደሚያደርግና ከታለመው ግብ እንደሚያደርስ አስተምረውናል::

# ያለቀለት ቤት ይጠብቀናል!

## ትርጉም በሻለቃ ግርማ ቡልቡላ

በእምነታቸው የጸኑ፣ የሀገራቸውን ህግ የሚያከብሩ፣ ግብር በመክፈል ለህዝባቸውና ለሀገራቸው ዕድገት የድርሻቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉና ቃላቸው ማተባቸው የሆነ ዜጎች ታሪክ ይማርከኛል። ሉዊ ሂልና ጄን የሰጡትን ምስምክርነት ዳግ ሂል “የእግዚአብሄርን ድምጽ እንዴት ማዳመጥ እንደሚቻል “ በሚለው መጽሃፉ ውስጥ “ያለቀለት ቤት ይጠብቀናል” በሚል ርእስ ያቀረበውን ጽሁፍ ሳነብ ልዩ ስሜት ስላሳደረብኝ፣ የጋራ የመግባቢያ ቋንቋዎችን ወደሆነው ወደ አማርኛ መለስኩት። መልካም ምንባብ፦

የሉዊ ሂል “ያለቀለት ቤት ይጠብቀናል” መጣጥፍ በጥበበ ነገር ወይም በአመክኖና በደመነፍስ ከልብ በመነጨ ዕምነት በምንቀበለው ሃሳብ መካከል ወዲያው ውጥረትን ይፈጥራል። ሂል አእምሮና ልብ፣ ስሜትና ሃሳብ ሳይጋጩና ሳይበጣበጡ ሊተባበሩ፣ ሊስማሙና አንዱ ለሌላው አጋዥ ሊሆን እንደሚችል ከራሱና ከትዳር ጉዋደኛው ከጄን ልምድ በመነሳት ያስረዳናል። በአእምሮና በልብ መካከል የመከባበር ሚዛን መኖር እንደሚገባም ያስተምረናል።

በኪራይም ሆነ በባለቤትነት መኖሪያ ለማግኘት በቂ ገንዘብ አልነበረንም።የተዳር ጉዋደኛዬ ጄን እኔ የምላትን ስለማትሰማኝ፣ ችግራችንን የበለጠ የተወሳሰበ አደረገው። አጣብቂኝ ውስጥ እንደገባሁ ይሰማኛል።

መሃንዲስና የተግባር ሰው ነኝ። የህንጻዎችንና የድልድዮችን ንድፍ (ዲዛይን) ከመስራቴም በላይ በሞያዬ ዩንቨርስቲ ውስጥ አስተምራለሁ። ተማሪዎቼም የተግባር ሰዎች እንዲሆኑ እሞክራለሁ። በዓለማዊ ስራዬ እንደምተጋው ሁሉ በመንፈሳዊ ህይወቴም በእግዚአብሄር ጽኑ እምነት አለኝ። ግን አምላክ ስለምድራዊ ህይወቴ እንዲያስተምረኝና እንዲመራኝ የምጠይቅና ድምጹንም በጸጥታና በእርጋታ የማዳምጥ አይደለሁም። ባለቤቴ ጄን ግን ስለማንኛውም ጉዳይ እግዚአብሄርን በጸሎት የምትጠይቅና የአምላክንም ድምጽ በእምነት የምታድዳምጥ ናት። ይህ የአሰራርና የአመለካከት ልዩነት አንዳንዴ በመካከላችን ችግር ይፈጥራል። በተለይም የዶክተርነት ትምህርቴን በኦሃዮ አጠናቅቄ ለማስተማር ወደ አሪዞና ክፍለ ሀገር ዩንቨርሲቲ ስመለስ ልዩነታችን አፍጥጦ መጣ። በመጨነቅና ግራ በመጋባት በባንክ ያለን ገንዘብ ቤት ለመከራየት እንደማይበቃን ስነግራት የተለመደ የፍቅር ፈገግግታ እያሳየችኝ፣ “እግዚአብሄር ያዘጋጀልን ያለቀለት ቤት ይጠብቀናል፣ ይሄንንም በቅርቡ ታየዋለህ” ትለኛለች ፈርጠም ብላ። እኔ ግን የሚታየኝ ተቃራኒው ነው። ሶስት ህጻናት ይዘን የጎዳና ተዳዳሪ እንዳንሆን ያሰጋኛል።

የዶክተርነት ዲግሪዬን ለማግኘት ለሁለት ዓመታት በኦሃዮ ስማር ጄንና ልጆቼ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል። ጥራት ያለው ኑሮ ለመኖር መማር እንዳለብኝ ያውቃሉ። የነጻ ትምህርት ስላገኘሁ የመማሪያ ክፍያ አልነበረብኝም። ሌላ የገቢ ምንጭ ስላልነበረን ለክፉ ቀን (ለክረምት) ያጠራቀምነውን ጥሪት አሙዋጠን በላነው። እስከመጨረሻው የመበደር አቅማችን ተበደርን።

ለጊዜው ባረፍንበት ሞቴል ጄን ልጆቻችንን ስታስተኛ በባንክ ያለንን ትንሽ ገንዘብ ማስላት ጀመርኩ።፡ጄን ልጆቹን አስተኝታ ወደ እኔ ስትመጣ ያለንበትን አሳሳቢ የገንዘብ ሁኔታ እንደገና አስረዳሁዋት። “ወደ ኦሃዮ ከመሄዳችን በፊት አሪዞና ውስጥ ቤት ያልተሰራበት ቁራጭ መሬት ተመልክተን ስንመለስ በቂ ለመነሻ የሚሆን ገንዘብ አጠራቅመን በዚይ አቁራጭ መሬት ላይ የምናልመውን ቤት ለመስራት መወያየታችን ትዝ ይልሻል?” አልኩዋት ተስፋ በቆረጠ ድምጽ። “አሁን ግን እንኩዋን የምናልመውን ቤት ለመስራት ማንኛውንም አይነት መኖሪያ ለመከራየት ገንዘብ የለንም” ጄን በጥሞና አዳመጠችኝ። የስጋት፣ የፍርሃትና የሽብር ንግግሬን ስጨርስ ቀስ ብላ በለሰለሰ ድምጽ “የምታስተምርበት ዩንቨርስቲ ደሞዝህን በቅድሚያ ሊከፍልህ አይችልም?” ስትል ጠየቀችኝ።

“ለሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ሊኖረን የሚችል ገንዘብ የለንም። ዩንቨርቲው በቅድሚያ አደመወዝ መክፈል ያለመክፈሉን አላውቅም” አልኩዋት፣ አሁንም ተስፋ በቆረጠ ድምጽ። ጄን እጇን በፍቅር ጠበቅ አድርጋ ጨበጠችኝና ውጥረቱንም ለማርገብ የሚከተለውን ተነፈሰች፣ “ለመልስ ጉዞ እቃዎቻችንን ስንቀረቅብ በባንክ የቀረንን ገንዘብ መጠን ሳይ ደንግጬ ነበር። ወዲያው እግዚአብሄር በጆሮዬ አንድ ነገር ሹክ አአለኝ። ‘ልጄ ጄን አአትጨነቂ፤ ያለቀለት ቤት ይጠብቅሻል’ ካነጋገሩ ቤቱን እግዚአእብሄር ራሱ የሰራው ይመስል ነበር።”

“ጄን እንደምታውቂኝ እኔ የተግባር ሰው ነኝ። በምኞትና ባልተጨበጠ ተስፋ እልኖርም። አንቺንም ሆነ እግዚአብሄርን መጠራጠሬ አይድለም። ጥበበ ነገርን/አመክኖን አፈርድሚ ከሚያበላ አመለካከት ጋር ችግር እንዳለኝ ታውቂያለሽ። ተጨባጩ ሁኔታ የሚያሳየን በባንክ ያለን ገንዘብ አንድ መቶ ሃምሳ ዶላር ብቻ መሆኑን ነው። ከአራዳ ርቆ የሚገኝ አፓርታማ ለመከራየት ለመጀመሪያን አለመጨረሻ ወራት መያዣ ካለን ገንዘብ ከሶስት እጅ በላይ ያስፈልገናል። እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ እንዴት ስለሚጠብቀን ያለቀለት ቤት እንነጋገራለን?” ጄን ስለዚህ ጉዳይ መከራከር አልፈለገችም። “ሂል! አሁን ደክሞናል፣ ከጥሩ እንቅልፍ በሁዋላ ነገ የሚሆነውን እናያለን።”

በማግስቱ የሚከራዩ ቤቶችን ማስታወቂያዎች ካነበብን በሁዋላ ፍለጋ ወጣን። ብዙ ማስነን አእቅማችንን የሚመጥን ቤት አጣን። እግረ መንገዳችንን ከዚህ በፊት የምናልመውን ቤት ለመስራት የተመኘነው ቁራጭ መሬት አሁንም ባዶ መሆኑን ተመለከትን። ለብባቤቱ ስልክ እንድደውልለት ጄን ጠየቀችኝ። “ለምን?” ስል በንዴት ጠየቅሁዋት። “ከዚህ በፊት ብዙ አድክመነውና አውከነው ቁራጩን መሬት አልገዛንም። ኣእንደገና በከንቱ ልናደክመው አይገባም።” “አእዝናለሁ፤ ሂል! ለባለመሬቱ ስልክ እንድንደውል መንፈሴ ይገፋፋኛል። የልቤ ትርታ ጥበበ - ነገርን ወይም አመክኖን የተከተለ አይደለም። ስልክ መደወል ካልፈለግህ ወደ ሞቴላችን ተመልሰን እራታችንን እንስራ።”

በሚቀጥለው ቀን ቅዳሜ እንደገና የሚከራይ ቤት ለማደን ተሰማራ። የተለየ ነገር አልነበረም። በማግስቱ እሁድ ለጸሎትና ለአምልኮ ወደ ቀድሞ ቤተ ክርስቲያናችን ሄድን። ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን ወዳጆቻችን እኛ ኦሃዮ በነበርንባቸው ዓመታት ወደ ሌሎች ቤተ ክርስቲያናት መዛወራቸውን ሰማን። በአሮጌው ቤተ ክርስቲያናችን ያገኘናቸው አዳዲስ ሰዎች በወዳጅነት ስሜት አስተናገዱን። የቤተ ክርስቲያኑም አለቃ አዲስ ነበሩ። የዕለቱን መለኮታዊ ትምህርት በዮሃንስ ወንጌል፤ ምእራፍ 14፤ ቁጥር 2 መሰረት አድርገው ጀመሩ። ጥቅሱ እንደሚከተለው ይነበባል። “በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ አለበለዚያ ግን የምትኖሩበትን ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ ባላልሁዋችሁም ነበር።”

“ካህኑ የግል ችግራችንን ተረድተው ትምህርቱን ለእኛ ያዘጋጁት ይመስላል” አለችኝ ጄን። ቤድንገት የመንፈስ ወቀሳ ወረረኝ፣፤ እስከዛሬ በእምነት የምፈልገውን ስላልጠየቅሁት ድምጹን ሰምቼ አላውቅም። ጄን ከእግዚአብሄር ጋር በምታደርገው ልዩና ልባዊ ቆይታ የሰማቺውን ስትነግረኝ አምክኖአዊ አይደለም በማለት ሳጣጥልባት ቆይቻለሁ። አእሁን ግን እግዚአብሄር ስለመኖሪያ ከካህኑ እንድሰማ አደረገ። የመጽሃፍ ቅዱሱን ጥቅስ የምጠራጠርበት ምክንያት አልነበረኝም። ጄንን በፍቅር አይን ተመለክትኩዋት። እጁዋን በታቀፈችው ልጃችን አሳልፋ የእኔን እጅ በመጨበጥ ጨመቅ አደረገቺው። ኣእኔም አጥብቄ ያዝኩዋት። ቃል ሳንተነፍስ ተግባባን።

የቤተ ክርስቲያኑ ስርዓት እንደተጠናቀቀ ኣእንደገአን ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ኑዋሪዎች የሚከራዩ ቤቶች ወደሚገኙበት ስፍራ ተጉዋዝን። የመጀመሪያና የመጨረሻ ወራት መያዣ ኣእንዲያልፋን ብንማጸንም የሚራራልን አጣን።

ወደ አረፍንበት ሞቴል ስንመለስ ከዚህ በፊት የምናልመውን ቤት ለመቀለስ በተመኘነው ቁራጭ መሬት በኩል አለፍን። ቁራጩ መሬት አሁንም ቤት አልተሰራበትም። “ለባለቤቱ ስልክ እንድንደውል የሚገፋፋሽ መንፈስ አሁንም አለ?” ስል ጄንን ጠየቅሁዋት። እራሱዋን በመነቅነቅ መስማማቱዋን ገለጠችልኝ። እኔም በዚያው ቅጽበት የመኖሪያችንን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሄር ተውኩት።

ወዲያው ወደ ቁራጭ መሬት ባለቤት ደወልኩ። ሰውየው በድምጼ አወቀኝ። በስልክ ኣእያወራን ከጠረጴዛው ስር ፋይሌን አውጥቶ ጉዳያችን እንዳልተዘጋ አረጋገጠልኝ፣ ፣ ቁራጩ መሬት በሚገኝበት ስፍራ በዚያው ሰዓት እንድንገናኝ ቀጠረን።

ስልኩን ሳልዘጋ ያንን ባለመሬት ኣእሁድ ከሰዓት በሁዋላ በከንቱ በማድከሜ የጥፋተኝነት ስሜት ወረረኝ። ያንን ቁራጭ መሬት ለመግዛት አቅሙ ስለሌለን ምን ልለው እንደምችል ግራ ገባኝ። ደግነቱ ከባለቤቱ ጋር ቁራጩ መሬት ባለበት ቦታ ስንገናኝ፣ዋናው ተናጋሪ እሱ ሆነ። ሰውየው የሚያወራው ስለቁራጩ መሬት አልነበረም። ኢላማዎቹ እኔና ጄን ነበርን። በዚያ ዓመት በዩንቨርስቲው ውስጥ ለማስተማር ውል መፈረም ያለመፈረሜን ጠየቀኝ። መኪናችንም ድሮ የሚያውቃት እንደሆነች ለእኛው መልሶ ነገረን። ስራ ትቶ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ በገንዘብ በኩል ጎጂና አእፈናቃይ እንደሆነ ጠቀሰ። ይህ ሁሉ ዳርዳርታ ቁራጩን መሬት ለመግዛት አቅም እንደሌለን ለማሳየት እንደሆነ ገባኝ።

“ትክክል ነህ፣ ስራ አቁዋርጦ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ቀላል አይደለም። ትምህርት ለመገብየት ያጠራቀምነውን ገንዘብ በልተነዋል። የእሁድ ከሰአት በሁዋላ የእረፍት ጊዜህን በከንቱ በማባከናችን ይቅርታ እንጠይቃለን። ይሄንን ቁራጭ መሬት ለመግዛት ምንም ገንዘብ የለንም። ደህና ሁንልን” በማለት የጄኔን እጅ ይዤ በመኪናችን አቅጣጫ መንገድ ጀመርኩ።

“ይህንን ገምቻለ”አለ ቤት እየሰራ የሚሸጠው ባለቁራጭ መሬት። ለዚህም ነው እዚህ እንድንገናኝ የቀጠርኩዋችሁ። ይህንን ቁራጭ መሬት ከስድስት ወራት በፊት ሽጬዋለሁ” አለን።

እንቆቅልሹ ስላልገባን ጉዞአችንን አቁዋርጠን ወደ ቤት ሰሪው አፈጠጥን።

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

# ቶሎሳኪያ፥ “ራ” ን በ“ላ” ይበውዙት!!

# ለጸረ-ማርያም ተንባላት የቀረበ ምግታር!)

ገሞራው - ስዊድን

ክፍል ሦስት - ካለፈው ዕትም የቀጠለ ..

ክቡራትና ክቡራን አንባቢያን፥ እንደምን ሰነበታችሁ:: ባለፈው የነሐሴ-መስከረምየሐዋርያእትም በዚህ ሰፊ ሀተታ በያዘ ዝግጅት ርዕስ ሥር ከተጨዋውትን በሁዋላ በሚከተለው መንፈስና የቤት ሥራ ጥያቄ ተለያየን:-

“ 'የክርስቶስ መለኮታዊ ኩነት፥ ከማርያም ሥጋና ነፍስ አልተዋሃደም!' ” ብለው የሚደርቁትን መናፍቃን በሚመለከት የጎረፈው “ተዋህዶአዊ” የቅኔ አዝመራ፥ በመጠንም ይሁን በአይነት ከቶ ይህን ያህላል ብሎ ለመናገር አይቻልም:: እንደው ለትይታው ያህል፥ አንዲት ታንኪረኛ የቅኔ ዘለላ እዚህ ብልጭ ባደርግ ደስ ይለኛል:: በታላቁ የዋሸራ ቤተ ቅኔ፥ ትምህርት ቤት ውስጥ

> “ኢትእመኑ ስብአ - እንዘ ትነብሩ በተድላ፤
> እሥመ ለማርያም ድንግል - ዘወለደቶ ቀተላ!!”

አንድ ወቅት ላይ የፈለቀች ናት:: የተጻፈችበት ስልት “አፍራሽ ቅኔ” ሲሆን፥ የቅኔ አይነትነቷም በመጠኗ አንጻር “ጉባኤ ቃና” ይባላል:: ይቺት!!

(የቅኔይቱን ትርጉም አፈላልጋችሁ ትረዱ ዘንድ ለአንባቢዎቸ እንደ የቤት ሥራ ሰጥቻለሁ::)

የቅኔዋን ባህርይ ትርጉም አግኝተናል የምትሉ ብትኖሩ የጥበባችሁንፍሬእንድትይልኩልን እያሳሰብን፥ ከዛሬ የሚቀትለው ምንባብ እነሆ፥ መልካም ቆይታ::

ነገረ ፅላት (ታቦት)

(ከዱር የሚቆረጥ ተራ ተክል አይደለም!)

“ላይችል አይሰጠው!” እንዲሉ፥ ጎይታ ቶሎሳ ጠበለ ሉተርን እስኪያቀረሻቸው ድረስ ሲከለብሱ አድረው ነው መሰለኝ፥ በነገታው ያ ደረዙር ሃንግአቭራቸው ገፋፍቶ ድንገት አስነስቱዋቸው፥ ምንም በማያውቁ ኢትዮጵያዊያን ላይ “ማርያምን ከጠራህ ያበድክ ነህ!.. የዱሩን እንጨት በመጥረቢያ ቆርጠውና ልገው ጨርቅ ካለበሱ በሁዋላ፥ ለሠሩት እንጨት ራሳቸው መልሰው ይሠግዱለታል … በኢትዮጵያ ምድር ምንጭ የሚባል ሳይኖር ከየትም የተገኙትን ተራ ፈሳሽ ውሃ፥ በልዩ ታእምር የፈለቀ ጠበል ነው እያሉ በማርያም፥ በአማኑኤል፥ በሚካኤል፥ በገብርኤል፥ (ብቻ እሱ እንዳይሰማዎት!) ይጋታሉ፥ ይጠመቁበታልም! ጎ በገዳማትና በአድባራት የሚገኙ፥ መናንያን ባህታዊያን ደናቁርት ናቸው! .. የተዋህዶ ሃይማኖት የድሪቶ ነት ባህርይ አለው'ነ ውዘተ.



ሃይሉ (ገሞራው)

በማለት የነቀፋና የስድብ ማዕበል አጉርፈውባቸዋል::

እኚህን ታላቅ አባትና መምህር፥ የግድ ማስተማር ይኖርብናል:: የማያውቁትን ነውና የተናገሩት በታቦት ልነሳ::

እኔ እንደምገምተው “ታቦት” የሚለውን ሰማያዊ ቃል አባት ቶሎሳ ትክክለኛ ትርጉሙን የሚያውቁ አይመስለኝም:: ቢያውቁ ኖሮማ “መጥረቢያ ይዘው ወደ ዱር ባልመረሹ ነበር!” ፥ ምንነቱን ለማስረዳት አስበው ማለቴ ነው:: ቶሎሳኮ ጭልጥ ብለው ተሳስተዋል:: “ስተዋል!” ብል ይሻል ይሆን? “ታቦት” የሚለው ሰማያዊ ቃል ትክክለኛና ቀጥተኛ ትርጉሙ “ሣጥን” ማለት ነው:: ለርስዎ በሚቀርበዎ ቁዋንቁዋ፥ :ሁቅብ: ማለት ነው:: ቁዋንቁዋውንም የራስዎን ቁዋንቁዋ ለመፃፍ በፊደሉ ይጠቀሙበት የለ! ሣጥን (ሳንዱቅ) የሆነ ነገር በውስጡ እንደሚያስቀምጥ ሁሉ ታቦትም እንደሳጥንነቱ የ“ፅላት” ማስ-ቀመጫ ነው:: ማህደርም እንደምንለው አይነት:: ይሁን እንጅ የእንጨቱ አይነትና የአሠራሩ ጥበብ ምለየቅሉ ነው:: እርስዎ ይዩ አይዩ በበኩሌ አላውቅም:: እኔ ግን ከመወጣትነት ሙያዬ ጋር በተያያዘ ምክንያት ብዙሃን የተለያዩ ጽላቶችን ለማየት ዕድል ገጥሞኛል:: ከንጹህ ዕብነ በረድ ተቀርጾ የተሠራ ልዩ ታቦት፥ ሄደው አያውቁ ይሆናል እንጅ ጋለሞታዎቹ ሴቶች መንደር “ውቤ በረሃ” አካባቢም ይገኛል:: በተለያዩ “ክቡር” ማዕድናትም የተሠሩ አሉ:: በብዛት ግን ከተለዩ እፀዋትና ተክሎ ችናቸው:: እንደዚያም ልበል እንጅ በፈጠርዎ ይሁንብዎትና የዱሩን እንጨት ሁሉ ታቦት ይሆናል ብለው እያውሩ:: ከሁሉም ከሁሉም አስቀድመው የፅላትንና የታቦትን ልዩነት ጠንቅቀው ማወቅ አለብዎ:: የሰማይና የምድሩን ርቀት ያህል ልዩነት አላቸው:: “ፅላት” የሚባለው ቃል የ“ጽሌ” ብዙ ቁጥሩ ነው:: “ፅሌ” የሚለው ቃል ራሱ የተገኘው “ጸለየ” ከሚለው ግሳዊ ቃል ነው:: ይሄስ እንዴት መጸለያ ሊሆን ቻለ? ዋናው ምስጢር እዚህ ላይ ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማንያን በየበዓላቱ ለታቦት ሲሰግዱ አይተው ከሆነ የሚሰግዱት ለታቦቱ አሌያም ለጽላቱ አይደለም:: ሃቁን ነው:: ማርያምን! ለታቦቱም ወይም ለጽላቱም አይደለም:: የሚሰግዱት በጽላቱ ላይ ተቀርጾና ተጽፎ ለተመዘገበው አሥርቱ ቃላት ነው! የተጻፉትን ቃላተ ህግ ከልባችን እናከብራቸዋለን፤ እንቀበላቸዋለንም:: ለማለት ነው የኔ ጌታ ቶሎሳኮ! ተግባባን? በቀጥታ ወደ መጽሃፉ ጥቅስ ልምጣ::

አበ ኦሪት የሚባለውን “ነቢዩን ሙሴ” አምናለሁ ያውቁታል:: በዓመተ ዓለም 1280 ላይ የነበረ ነው:: አዶናይ ፊለፊት በገሃድ ቀርቦ ያነጋግረው የነበር ቅዱስና ብቁ አባት ነበር::

“አሥርቱ ቃላት በሁለቱ ጽላቶ ች ላይ በእግዚአብሔር ጣት ተጻፈ:: እነዚህም የምስክር ጽላቶ ች ተባሉ:: (ዘጸአ. 31፥ 18፥ 34 . . .)

“ሙሴ ከግራር እንጨት ታቦትን እንዲሠራ ታዘዘ አሠራሩም ሣጥን አይነት ነበር . . . ታቦቱ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ነበር” (ዘጽእ. 25-1፥ 1-22፥ 40-20)

የዚያ ዘመኑ ታቦት የሚከተለው አይነት ነበር ይኸውልዎ - በምላስዎ ይዩት! በአንደበትዎ ወደፊት እንዲመሰክሩለት::

ብዙሃን ዝርዝር ነገር ውስጥ ሳልገባ፥ በኢትዮጵያዊው የሃይማኖት ይዘታዊ ተቁዋማት ውስጥ ከዕፅ ጋር የተያያዙና ጥብቅ ዝምድና ያላቸው ዕሴቶ ች ሁሉ መሠረታዊ ምንጫቸውና ጥንታዊ መገኛቸው አንደ ነው:: የዚህም መገኛ ምንጭ ታሪክ ተጽፎ የሚገኘው ከ “ታሪክ-ዕፅ መስቀል” ሃተታ ላይ ነው:: ተክለ-ነክ ያላቸው ኩነቶች ሁሉ፥ እኔ ምንጊዜም አዛምጄ የማቀርባቸው ከዚሁ ታሪክ ጋር ካገኘሁት ትንግርታዊ ማስረጃ ጋር ነው:: የዚህም ልዩ ታሪክ ሃተታ እንደሚተርከው ሃቅ ከሆነ ይህ ዕፅ ምድራዊ አይደለም:: “ምድራዊ ነው!” ሊባል የሚችለው፥ እዚሁ ምድራችን ላይ የተገኘ ቢሆን ነበር:: ጽሁፍ እንደሚለው ከሆነ፥ ዕፁ የርተገኘው ከምድራችን እርከን ላይ ከፍ በማለት “ረብባ” ከምትገኘው ሕዋ ላይ ነው:: ይችም ቦታ የምትጠራው በሚያባብል ስሙዋ “ገነት” እየተባለች ነው:: ቅፅል ሲጨመርላት ደግሞ፥ “ብሀረ ጻድቃን” አለያም፥ “ምኩራበ ቅዱሳን” እ ያ ለ ‐ ያ ሽ ሞ ነ ሙ ኑ ዋ ታ ል : : እጅግ ሲበዛ “ውብ ናት”ም እያሉ ያልሚቅካሹዋታል:: ለምናልባቱ ይህን “ሃቀኛ” ታሪክ የምትጠራጠሩ ብትኖሩ፥ ድርሳኑ ተጽፎ የሚገኘው በአንደምታው ቅዳሴ እትም ውስጥ፥ ከኪዳን ዘነግህ ክፍል ላይ ነውና ለማገናዘብ ሞክሩ::

መረዳት ለሚፈልግ ቅንና ብሩህ ህሊና፥ ትንግርተኛው ድርሳን የሚከተለውን ያንብቡልኝ!!

“. . . ታሪክ፥ ዕፅ መስቀልን ከዚህ ይሰበስባሉ፤ ሳኦ ልጁ ቢታመምበት ፈላስፎች ሰብስቦ መድሃኒት እንዲፈልጉ ጠየቃቸው:: እነሱም የማይቻላቸው ቢሆን ለእኛስ አይቻለነም፥ የ ንሥር ዕንቁላል አስመጥተህ ከግንብህ አስገብተህ ዝጋበት:: ንሥር ልጁ እዚያ እንዳለ አውቆ ከገነት ዕፅ ቆርጦ አምጥቶ ከግንቡ ላይ ይጥለዋል::

ልም፡፡እንዴው ለትይታው ያህል አንዲት ታንኪረኛ የቅኔ ዘለላ እዚህ ብልጭ ባደርግ ደስ ይለኛል፡፡በታላቁ የዋሸራ ቤተ ቅኔ ትምርት ቤት ውስጥ አንድ ወቅት ላይ የፈለቀች ናት፡፡የተጻፈችበት ስልት ''አፍራሽ ቅኔ'' ሲሆን፣የቅኔ አይነትነቷም በመጠኗ አንፃር ''ጉባዔ ቃና'' ይባላል፡፡ይቺት !!

''...ኢትእመኑ ሰብአ - እንዘ ትነብሩ በተድላ፣
እስመ ለማርያም ድንግል - ዘወለደቶ ቀተላ!!...''

(የቅኔይቱን ትርጉም አፈላልጋችሁ ትረዱ ዘንድ፣ለአንባቢዎቼ እንደ ቤት ሥራ ሰጥቻለሁ)



ቶሎሳኮ !

ይህን ሥዕል፣በሙሉ አመለካከትዎ፣በዓአይነተ ልቡናዎ በጥሞና እንዲመለከቱልኝ እጠይቃለሁ፡፡ ለመሆኑ እንዲህ ሲያዩት ምን ይመስልዎታል ? ያ በግላዊ አስተያየትዎ፣''ያ የሰላ መጥረቢያ ወደ ዱር ይዞ ይገባና ቆርጦ ቆርጦ ተሸክሞ ቤቱ ከመጣ በሂላ፣እንደሚፈልገው አይነት ጠርቦና ልጎ ካዘጋጀ በሂላ፣ታቦት ነው በማለት ሱቲ አልብሶ የሠግድበታል!'' ያሉት ዕቃ ይሆን ? በርግጥም ነው ብለው ካመኑ፣ዝርዝሩን መግለጫ፣ከዚህ በሚከተሉት ገጾች ላይ ሠፍረው የሚገኙትን የነጠሩ ሃቆች ይማሩባቸው!

ለታቦት፥ ለመስቀል፥ ለማህተመ መስዋዕትና ለቀሩትም ተክለ-ወጥ የቤተ ክርስቲያን መገልገያዎች ሁሉ የምንጠቀመው (ሌላ ችግር ካልተፈጠረ በስተርቀር) ከዚህ ዕፅ በተገኘ ተክል ነው::

እንግዲህ “ሃቆች” በዚህኛው ዘርፋዊ ምንጭ ላይ ነጥረው የተቀመጡ ከሆነና ማስረጃነቱም “ሰሐ” የማይወጣለት ከሆነ፥ እነ አባት ቶሎሳኪያን “. . . ስለ መጥረቢይ ሮይዞ ወደ ዱርና ወደ ጭእካ በመግባት ቆርጠና መንጥሮ በማምጣት የሚጠቀሙበት ተክል ሁሉ ሺ ጊዜ ይላግ ይጠረብ እንጅ “ታቦት” ላይሆን ነው!” (ቂ! ቂ! ቂ!)

ለክፉም ለደጉም ታሪኩን አንብቦ ግንቡ ይሰነጠቃል፥ ዕንቁላሉን ይዞ ይሄዳል፤ በዚህ ልጅህ ይፈወስልሃል አሉት:: ንጉሥ ላስፈልግ ባለ ጊዜ የሚቸግረው የለምና፥ አስፈልጎ አምጥቶ ከግንቡ አስገብቶ ዘጋበት:: ንሥር ዕንቁላሉ እዘዚይ ሮእንዳለ አውቆ፥ ከገነት ዕፅ ቆርጦ አምጥቶ ጣለበት:: ግንቡ ተሰነጠቀ፤ ዕንቁላሉን ይዞ ሄደ፤ ብዚያ ልጁ ተፈውሶለታል:: ይህም ዕፅ ገባሬ ታእምራት ነው:: ወደ ዮርዳኖስ ሲሄዱ ሰዎች አግኝተው በጽንፈ ዮርዳኖስ ተክለውታል:: ሰለሞን ቤተ መቅደስን ሲሠራ አስቆርጦ አምጥቶታል:: መቃን ቢያደርጉት አጥሮባቸው፥ ጎበን ቢያደርጉት ረዝሞባቸው እንዳይቆርጡት እንጨቱ መልካም

ወደ ገጽ 23 ዞሯል

# "ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ" እንዳይሆ

## ከደረጀ ጎሹ በላቸው

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና አርትራዊያን መካከል የመወያያ ርእስ ሆኖ ያለው የኢትዮጵያና የኤርትራ የወደፊት እድልና ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበት በተደረጉ ውይይቶች በኢትዮጵያ በኩል ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴና በኤርትራው ምሁር ፕሮፌሰር ፍስሐጽዮን መድህኒሄ ተዘጋጅተው የቀረቡት አነጋጋሪና አወያይ ጉዳዮች ናቸው።

ኢትዮጵያንና ኤርትራን በምን አይነት መልክ ማገናኘት ይቻላል ለሚለው ርእስ ሁለቱ ምሁራን የየበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተዋል። ሁለቱም ምሁራን በሁለቱም ሀገሮች አንድነትና ውህደት የሚያምኑ ሲሆን ልዩነቶቻቸው ፕሮፌሰር ዳንኤል የሁለቱ አገሮች ውህደት "በፌዴሬ ሽን" ይሁን ሲሉ፥ ፕሮፌሰር ፍስሐጽዮን ደግሞ "በኮንፌደሬሽን" ይሁን ነው የሚሉት።

ምሁራኑ ይህንን አብይ ጉዳይ ሲያነሱ ከሁለቱ ሀገሮች ፍቺ በሁዋላ በሕዝቦቻቸው መካከል የተደረጉትን ጦርነቶች፥ አሁን ያሉበትን ውስብስብ ችግሮች በማየትና ለነዚህ አላስፈላጊ በሁሉም አቅጣጫ የሕዝቦቻቸውን ሁለንተናዊ እድገት ማነቆ የሆነውን ችግር ለማስወገድና ሕዝቡን ለተሻለ እድገት ለማብቃት ዋናው መንገድ ይህ ሊሆን ይችላል ብለው አስበው ሊሆን ይችላል። ይህ የኔ ግምት ሲሆን ሌላውን እዚህ ላይ ላቁምና ወደተነሳሁበት ጉዳይ ልመለስ።

ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌደሬ ሽንም ሆነ በኮንፌዴሬሽን ከመዋሃዳቸው በፊት መከናወን ያለበትና እልባት ሊያገኝ የሚገባው አንድ ጉዳይ አለ። ይኸውም የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ የባህር በር ያስፈልጋታል። በቀድሞ የስም አጠራሩ ባህረ ነጋሽ የአሁኑ ቀይ ባህር ባለቤት የነበረችው አገራችን ኢትዮጵያ ይህንን ባህር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በባለቤትነት ይዛው እንደነበረው በተለይም ከፍተኛ የ ንግድ እንቅስቃሴ ይደረግበት እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ መብቷ ተነፍጉዋት ወደብ አልባ ከመሆኑዋም በላይ በዚሁ ምክንያት ከፍትህ ማጣትና በነጻነት ካለመኖር ባሻገር ለኢኮኖሚያችን መቆርቆዝ ዋነኛው ምክንያት ሆኗል። ይህ እንደስሙ ትርጉዋሜ በኢትዮጵያዊያን ደም የቀለመው ቀይ ባህር የህልውናችን ዋነኛው መሠረት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እሱ የመረጠው መንግሥት እስኪመጣና በባህሩ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት እስከሚያስጠብቅለት ጊዜ ድረስ ጥያቄው በውስጣችን ውስጥ ተዳፍኖ የሚኖር ለእውነተኛ ባለቤቱ እስካልተመለሰ ጊዜ ድረስ ህያው ጥያቄ ሆኖ ይኖራል። ለዚህም ነው የኢትዮጵያና የኤርትራ የወደፊት እድል ዘወትር በጥያቄ ምልክት ውስጥ ያለው። ስለሆነም ከሁለቱ ሀገሮች ውህደት በምንም መልኩ ይዋህዱ ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ መፍትሄ ያግኝ ስል በሁለት ምክንያቶች ነው። ይኸውም፦

ያለፍላጎቱ በገንጣዮችና አስገንጣዮች ጦርነት ከእናት ሀገሩ፥ ከዚያም አልፎ ከወገኑ ከጎሳው እንዲለይ የተፈረደበት አሰብ እስከ ምጽዋ የሚኖረው የአፋር ሕዝብ ተለያይቶ መኖር የለበትም። የሰው ልጆች መገኛ የሆነው የአፋር ሕዝብና ክልል ለባለመብቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መመለስ አለበት።

የኢትዮጵያየባህር ባለቤትነት ከተረጋገጠ ሁለቱም ሀገሮች፥ ማለት ኢትዮጵያና ኤርትራ የባህር በር ባለቤቶች ስለሚሆኑ የሁለቱ ሀገሮች ግንኙነት አንዱ ከሌላው ጥቅም ለማግኘት የተደረገ ሽስቅያስመስለው በኮንፌሡዴሬ ሽንም ከሆነ አንዱ ከሌላው የሚጠብቀው ነገር ስለሌለ በፌዴሬሽን ለመዋሃድ መንገዱን ያፋጥነዋል። በፌዴሬሽንም ከሆነ ፌዴሬሽኑን የጸና መሠረት ላይ ስለሚያቆመው ዘላቂነት ይኖረዋል።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ዛሬ ቢለያዩምና የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎችንም ቢያውለበልቡ ሕዝቡ በባህሉ አንድ አይነት ነው፤ አበላሉ፥ አለባበሱ፥ ሰላምት ሮአሰጣጡ፥ እምነቱ የሚያከብረው በግል ቁዋንቁዋው የጽሁፍ ፊደላት ከዚያም አልፎ እስከ አሁንም ኤርትራ ውስጥ እየተቀመጠ ኢትዮጵያዊያን ነን ብለው የሚያምኑ ኤርትራዊያንን ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ኤርትራ ውስጥ ተዋልዶ ተጋብቶ የኖረውና ሁሉም ያለውን ችግር በመፍራት ለራሱ ምንነቱን አምቆ የያዘውን ቁጥር ስናይ ሎስመለያየት የደረሱት በፍላጎታቸው ነው ለማለት አያስደፍርም።

ወያኔ ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ ካደረጋት በሁዋላ፥ በሁለቱ ሀገሮች የተፈጠረው የድንበር ግጭት ምን ያህል ወገኖቻችን እንዳለቁ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ድጋሜ ጦርነት ውስጥ መግባትን አንፈልግም። ተለያይተንም መቆየቱን ከመረጥን ወደ ጦርነት ሊወስዱን የሚችሉ ነገሮች በሙሉ ተጠንተው በሁለቱም ሀገር ሕዝቦች ቅን አመለካከት መወገድ አለባቸው። ሁላችንም በሰላም መኖር እንፈልጋለን። ስለዚህ ወደዚህ የጦርነት አዙሪት ውስጥ እንዳንገባ ከውህደቱ በፊት የኢትዮጵያ የባህር በር መፍትሄ ያግኝ። ካለበለዚያ ይህንን ሳንፈታ ውህደት ውስጥ ከገባን አንድ ጉልበተኛ ተነስቶ ለብቻችን እንሆናለን ካለ ሌላ የጦርነት አዙሪት ውስጥ መግባታችን ነውና ከውህደቱ በፊት የባህር በራችንን እናስመልስ። "ዳቦ ተቆረሰ ጨዋታ ፈረሰ፡ እንዳይሆን።

# የኒው ዮርክ ቤተ መጽሐፍ ማህበር ዓመታዊ የ ንግድ ትዕይንትና ኮንፈረንስ አካሄደ፤

ከገጽ 2 የዞረ

መኖር እንዲችል እንዴት ሊያግዙ ይችላሉ የሚለው እንደኛው ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ማህበረሰባዊ የህትመት ውጤቶች የወደፊት ዕድል ምን ይመስላል፥ ወደፊት መቀጠል ይችላሉ? የሚል ነበር።

የሐዋርያ ወኪል በመወያያ ርእሶች ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው ገለጻ የሰጠባቸው ሲሆን፥ የሐዋርያን አጀማመርና የረጅም ዓመታት ሁለገብ የአገልግሎት ተግባሮች መነሻ አድርጓል። ሰሜን አሜሪካ ሕዝባዊ መሠረቱ ከተለያዩ ሀገሮችና ባህሎች የመጡ የሰው ልጆች የሰፈሩበት ክፍለ ዓለም መሆኑን የገለጸው ወኪል፥ የመድበለ ማህበራዊ የህትመት ውጤቶችና የሌሎቹም የብዙሃን መገናኛዎች (ራዲዮ፥ ቴሌቪዥን..ወዘተ) ጠቀሜታና አገልግሎት ቢያንስ በሦስት ደረጃዎች ሊጠቃለል እንደሚችል አመላክቷል። ይኸውም፥ 1ኛ) ከእናት ሀገራችን ጋር ግንኙነታችን እንዳይቋረጥ፥ 2ኛ) በምንኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ እንደ ድልድይ ሆኖ ለማገልገል፥ 3ኛ) ማንነትን ለመጠበቅና በፖለቲካ፥ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ገጽታዎች ኮሚኒቲው ጥንካሬ እንዲያገኝ ያግዛሉ የሚል ሲሆን፤ የማህበራዊ ህትመት ውጤቶችን የወደፊት እጣ ፋንታ በተመለከተ ደግሞ የህትመት ውጤቶቹ ያለባቸውን ከባድ ችግር ጠቅሶ ነገር ግን የማህበረሰቡ የዘወትር አይንና ጆሮ በመሆናቸው እንደ ማህበረሰቡ እድገትና ድክመት አብረው የሚቀጥሉ መሆኑን አትቷል። በችግር ደረጃ ከተጠቀሱት መካከል የኢንተርኔት ግኝትና መስፋፋት አንዱ ሲሆን፥ የአዲሱ ትውልድ ከባህሉና ከአገሩ መራቅ ደግሞ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑ ተጠቅሰዋል።

በእነዚህ ነጥቦችና ሌሎቹም ተናጋሪዎች በሰጧቸው ጠቃሚ መንደርደሪያዎች ላይ በመነሳት ተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ያካሄዱና ጠቃሚ ተመክሮዎችን የተለዋወጡ ሲሆን፥ በኮንፈረንሱ አዘጋጆች በኩል ከፍተኛ አድናቆትን አትርፏል። ከሁሉም በላይ ሐዋርያ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷት ነበር። ሌሎች ሁለቱ የህትመት ውጤቶች የሚዘጋጁት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን፥ ሐዋርያ ግን መሠረቷን ባህላዊ ቋንቋዋን በማድረጓ ለኮንፈረንሱ የውይይት ዓላማ የገጠመ ነበር። ሁሉም ተወካዮች በተ-ላለፈው መልእክት መሠረት የህትመት ውጤቶቻቸውን ቅጂዎች ይዘው መጥተው ስለነበር ለኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች እይታ ቀርቧል።

# የካናዳ ብሄራዊ የህዳጣን ህትመትና መገናኛ ምክር ቤት የሊበራሉን ፓርቲ መሪ አስተናገደ!

ከገጽ 1 የዞረ

ይህ ሁለተኛ ጊዜያቸው ሲሆን፥ በዚህ ስብሰባ እንዳለፈው ስብሰባ ሁሉ አስቀድመው ያማረሩትና በስም ሊጠሩት ያልፈለጉት ጉዳይ ቢኖር 'ኢትኒክ' (Ethnic) የሚለውን መገለጫ ነው። እንደመሪው አመለካከት በካናዳዊነቱ የሚበላለጥ ትንሽና ትልቅ ካናዳዊ ስለሌለ ይህን ቃል ብጠቀም ዜጎቼን አሳንሼ የተመለከትሁ ይመስለኛል ብለዋል። በተለያዩ ርዕሶች መግለጫቸውና የጥያቄና መልስ ልውውጦቻቸው ላይ እየደጋገሙ እንዲያዝላቸው ባስደመጡት ንግግራቸው፥ "አንድ ካናዳዊ፥ ካናዳዊ ነው፥ ካናዳዊ ነው፥ አዎ ካናዳዊ ነው!!" (a Canadian is a Canadian, a Canadian, and a Canadian!) የሚለው የዕለቱ ሃይለ ቃላቸው ነበር። በተለይማ፥ ዜግነታቸው ካናዳዊ የሆኑ የማህበረሰብ አባላት ወደየትውልድ አገሮቻቸው ወይም የሥራ ጉብኝትና ወዳጅ ዘመድ ለመጠየቅ ወደተለያዩ የዓለም አካባቢዎች ሲጉዋዙ በየደረሱበት ሀገር በጨካኝ እጆች ላይ ወድቀው ስለሚቸገሩና ደራሽ ስለሚያጡ ካናዳዊያን ሲናገሩ በስሜት ይዋጣሉ።

ሚ/ር ኢግናቴፍ (Mr. Ignatieff) ትኩረት ሰጥተው ገለጻ ከሰጡባቸው ጉዳዮች መካከል የኢኮኖሚው ግስጋሴና ሥራ አጥነት ችግር፥ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት፥ ትምህርትና ጤናን አስመልክቶ ሰፊ ገለጻ ያደረጉ ሲሆን የዓለም ህብረተሰብን ባህርያት አካታ የያዘችው ካናዳ በዓለም አቀፍ ግንኙነቱዋ ብዙ ልትሰራ እንደምትችል ያላቸውን ጥልቅ እምነት ገልጸዋል። ከሞላ ጎደል የመላው ዓለም ቁዋንቁዋዎች ካናዳ ውስጥ ይነገራሉ ያሉት መሪ፥ ዜጎቻችን ካናዳ እንደ ህንድና ቻይና ከመሳሰሉ ሀገሮች ጋል ለሚኖራት የንግድ ግንኙነት በቀላሉ በመግባባት አብይ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ብለዋል።

ዓለምአቀፍግንኙነትንበተመለከተ ልዩ ልዩ ጥያቀዎች ቀርበውላቸው ማብራሪያሰጥተዋል። ከዚህም አኩዋያ፥ በየሀገሮች የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ጥያቄ፥ የአውዳሚ የጦር መሳሪያዎችን እሽቅድድም በተመለከተ፥ በውይይት ሂደት ላይ ስላሉ ታላላቅ አለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ከፓርቲያቸው አቋዋም አኩዋያ ማብራሪያ ሰጥትዋል።




Tikam K. Lalla, LL.B.

• BARRISTER • SOLICITOR • NOTARY PUBLIC

•ኢሚግሬሽን •ቪዛ •የህግ ውክልና

• House Purchase/Sale/ Mortgages
• Wills • Incorporation • Business
• Immigration • Visa • Declarations
• Power of Attorneys • Notarizations

ቲካም ኬ ላላ፥ የህግ ጠበቃ

Toronto Main Office:
1203B Bloor St. W., Toronto, ON, M6H 1N4
(Between Lansdowne & Dufferin)
Tel: 416-532-2801 • Fax: 416-532-4942
email: tklalla@rogers.com

Mississauga Home office:
5159 Hidden Valley Court
(Eglinton & Creditview)
Tel: 905- 812-8004
(Evening & Weekends - By appointment only)

# FOSSIL FINDS EXTEND HUMAN STORY



An impression of what "Ardi" would have looked like based on the fossil finds

By Jonathan Amos
Science reporter, BBC News

**An ancient human-like creature that may be a direct ancestor to our species has been described by researchers.**

The assessment of the 4.4-million-year-old animal called *Ardipithecus ramidus* is reported in the journal Science.

Even if it is not on the direct line to us, it offers new insights into how we evolved from the common ancestor we share with chimps, the team says.

Fossils of A. ramidus were first found in Ethiopia in 1992, but it has taken 17 years to assess their significance.



Natural History Museum's Professor Chris Stringer: "The skeleton is very primitive"

The most important specimen is a partial skeleton of a female nicknamed "Ardi".

If Ardipithecus ramidus was not actually the species directly ancestral to us, she must have been closely related to it The Ardipithecus project team

The international team has recovered key bones, including the skull with teeth, arms, hands, pelvis, legs, and feet.

But the researchers have other fragments that may represent perhaps at least 36 different individuals, including youngsters, males, and females.

One of the lead scientists on the project, Professor Tim White from the University of California, Berkeley, said the investigation had been painstaking.

"It took us many, many years to clean the bones in the National Museum of Ethiopia and then set about to restore this skeleton to its original dimensions and form; and then study it and compare it with all the other fossils that are known from Africa and elsewhere, as well as with the modern age," he told the journal.

"This is not an ordinary fossil. It's not a chimp. It's not a human. It shows us what we used to be."



### Tree life

The fossils come from the Middle Awash study area in the Afar Rift, about 230km northeast of Addis Ababa, Ethiopia's capital.

Some of the characteristics of the animal's skeleton are said to echo features seen in very ancient apes; others presage traits seen in later, more human-like species.

The scientists say 1.2m-high (4ft) Ardi was good at climbing trees but also walked on two feet. However she did not have arched feet like us, indicating that she could not walk or run for long distances.

"She has opposable great toes and she has a pelvis that allows her to negotiate tree branches rather well," explained team-member Professor Owen Lovejoy, from Kent State University, Ohio.

"So half of her life is spent in the trees; she would have nested in trees and occasionally fed in trees, but when she was on the ground she walked upright pretty close to how you and I walk," he told BBC News.

That she lived in what would have been a wooded area 4.4 million years ago is somewhat challenging, says the team. It had been thought that early human evolution was driven, if only in part, by the disappearance of trees - encouraging our ancestors to walk on the ground.

"These creatures were living and dying in a woodland habitat, not an open savannah," said Professor White.

Because of its age, Ardipithecus is said to take science closer to the yet-to-be-found last common ancestor with chimps, our close genetic relatives. And because many of Ardipithecus' traits do not appear in modern-day African apes, it suggests this common ancestor may have existed much further back in time than had previously been supposed - perhaps seven or nine million years ago.

Comparisons with modern chimp and gorilla anatomy also underline just how much these African apes themselves have evolved since parting company with the line that led eventually to modern humans.

### Rapid evolution

Asked whether A. ramidus was our direct ancestor or not, the team said more fossils from different places and time periods were needed to answer the question.

"We will need many more fossil recoveries from the period of 3-5 million years ago to confidently answer that question in the future," the scientists said in a briefing document that accompanied their journal papers.




"But if Ardipithecus ramidus was not actually the species directly ancestral to us, she must have been closely related to it, and would have been similar in appearance and adaptation. It has been a 17-year investigation to assess the discoveries Independent experts in the field are struck by how primitive Ardipithecus appears compared with the Australopithecines, another group of hominid (human-like) creatures from Africa that lived slightly nearer to us in time.

One species in particular, Australopithecus afarensis, the famous "Lucy" fossil found in 1974, is very strongly linked into the human story because of its developed walking ability. For Ardipithecus ramidus to also sit on that direct line seemed to require some rapid evolutionary change, commented Professor Chris Stringer from London's Natural History museum.

"With Australopithecus starting from four million years ago, one would have thought that things would have moved further down the line by 4.4 million years ago," he told BBC News.

"OK, you can have very rapid change, perhaps; or Ardipithecus might be a residual form, a relic of a somewhat older stage of evolution that had carried on. Perhaps we will find something more like Australopithecus at 4.4 million years old somewhere else in Africa."

Jonathan.Amos-INTERNET@bbc.co.uk



# HUMAN RIGHTS WATCH HONORS TOP RIGHTS DEFENDERS

## DEFENDERS WORK TO END ABUSES IN BURMA, CONGO, ETHIOPIA, AND RUSSIA

**Bo Kyi, Burma**

These extraordinary individuals confront tremendous challenges every day, yet they work selflessly to end human rights violations and bring abusers to justice. We hope this award, named for Alison Des Forges, will inspire and protect them as they struggle to uphold human rights in their countries.

Kenneth Roth, executive director of Human Rights Watch

(New York) - Four courageous and tireless advocates of human rights - from Burma, Democratic Republic of Congo, Ethiopia and Russia - have been awarded the prestigious Alison Des Forges Defender Award for Extraordinary Activism, Human Rights Watch said today. The four work to uphold freedom of expression, to protect women in conflict, and to ease the plight of political prisoners, despite threats and persecution from the authorities.

The awards are named for Dr. Alison Des Forges, senior adviser to Human Rights Watch's Africa Division for almost two decades, who was tragically killed in a plane crash in New York on February 12, 2009. Des Forges was the world's leading expert on Rwanda, the 1994 genocide and its aftermath, and Human Rights Watch's annual award honors her outstanding commitment to and defense of human rights.

The four winners of Human Rights Watch's 2009 Alison Des Forges Defender Award for Extraordinary Activism are:

Daniel Bekele, lawyer and activist from Ethiopia;

Bo Kyi, co-founder of Burma's Assistance Association of Political Prisoners;

Elena Milashina, reporter for Novaya Gazeta, Russia's leading independent newspaper; and

Mathilde Muhindo, women's rights activist working to stop sexual violence in Democratic Republic of Congo.

"These extraordinary individuals confront tremendous challenges every day, yet they work selflessly to end human rights violations and bring abusers to justice," said Kenneth Roth, executive director of Human Rights Watch. "We hope this award, named for Alison Des Forges, will inspire and protect them as they struggle to uphold human rights in their countries."

Human rights defenders are critical partners for Human Rights Watch staff conducting investigations in more than 80 countries around the world. The award winners will be honored at the 2009 Human Rights Watch Annual Dinners in Chicago, Geneva, Hamburg, Houston, London, Los Angeles, Munich, New York, Paris, San Francisco, Santa Barbara, Toronto, and Zurich.



DANIEL BEKELE 2008 Morag Livingstone

**Daniel Bekele, Ethiopia**

In the ever-shrinking space for freedom of expression in Ethiopia, Daniel Bekele, a prominent anti-poverty activist and human rights lawyer, has faced heavy-handed government repression. After leading a grass-roots effort to promote voter education and participation in Ethiopia's controversial 2005 parliamentary elections, as well as election monitoring and reconciliation after the vote, Bekele was arrested and spent two-and-a-half years in prison on charges of inciting violence against the government. Human Rights Watch honors Bekele who, at great personal risk, challenges the Ethiopian government to uphold the civil and political rights that protect all people.



BO KYI © 2008 Patricia Williams

**Bo Kyi, Burma**

It is important to know that Ethiopians will enter unwittingly the Second phase of this continued destruction when the May 2010 election is about to take place. The plan is to leave Ethiopians without any hope of change, and with no chance of a way out from the devilish poverty and brutal oppression. Let us examine the humans' choices and deeds from these perspectives: If a man crosses in front of a moving car, he would shorten his life. If a man decided to spend the night outside his home when the beasts take over the village, he has decided to shorten his life. God has nothing to do with those decisions. Respectively, Ethiopia is questioning the passion of this generation in ways that it never did of any of its children through the ages. Ethiopia is demanding those whom she fed/raised to pay her back so that she can reach the next generation. The leaves, roots, and rocks of Ethiopia must yield the medicine that will eradicate the carrier of Kilil virus.

•••

**Note**

The author appreciates well thought comments, views and suggestions. The comments will be added with this document 'as is' and be forwarded to the committee that may be formed to study the practicality of this proposal.

The critical reviews and information obtained from experts has made this proposal possible, and their contributions and willingness to advance this study to the next level has been profoundly encouraging.

•••


ስለ ጸሐፊው፦

ዘውገ ፋንታ ከቀድሞው ኃ.ሥ.ዩ ሕንፃ ኮሌጅ ዲፕሎማ ተቀብሏል። ከዚያም፣ ዩ.ኤን. በሰጠው ስኮላርሺፕ በኢትዮጵያ መንግሥት ተመርጦ፣ በኢንግላንድ ስለ ጂኦደቲክ ሰርቬይስ እና ካርቶግራፊ የተሰጠውን ከፍተኛ ትምሕርት አጠናቆ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ፤ በመሬት ይዞታ አስተዳደር ሚኒስተር በካርታ ድርጅት ክፍል በሲንየር ካርቶግራፈር ደረጃ ተመድቦ አሜሪካ ለትምህርት እስከ መጣ ድረስ ሀገሩን በሙያው አገልግሏል።

የሀገር ከፍተኛ ዕቅዶች ላይ እየተመደበ ሰፊ አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ የሀገርን ሀብትና ቅርስን የሚመለከቱ አያሌ ምስጢራዊ ስራዎች ይገኙበታል። ከዓለም ባንክ ባለሙያዎች ጋር ኢትዮጵያን ወክሎ ሰሜን ግዛት (ኤርትሪያ፣ ትግራይ፣ ቤገምድር፣ ጎጃምና ወሎ) ዕድገት እርምጃ ዕቅድ፣ የመሬትንና የሕዝብን አሰፋፈር ጥናት በተጠቀሱት ቦታዎች በመዞር፣ በመቀየስና ሰፊ የምድረ ገጽን ዝርዝር በመሰብሰብ የልማት ጥናት አጠናቋል። የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ክልል በሁለቱ አገሮች ስምምነት ሲደረግ፣ በውጭ ጉዳይ ምንስቴር ውስጥ ተመድቦ፣ እጅግ ምስጢራዊ የሆኑትን ጉድዮች በታላቅ ጥንቃቄ ይዞ በተሰጠው መመሪያ መሰረት አስፈላጊ የስምምነት መፈራረምያ የሆኑትን ካርታዎችን አዘጋጅቷል።

በግሉ የመጀመሪያውን የአዲስ አበባና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ካርታዎች አሳትሟል። የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ፕሮፌሺናል ካርቶግራፈር የተባለ ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ፣ እንግሊዝና አሜሪካ መንግሥቶች የአገልግሎት ምስክርና የሙያ ማረጋገጫ ሽልማቶች ተቀብሏል።

አሜሪካ መጥቶ የባችለርና ማስተርስ ፕሮግራሙን አከናውኖ፣ በተለያዩ የመንግሥትና የኩባንያ ድርጅቶች ሰፋ ያለ አገልግሎት ሰጥቷል። የስያትል ከተማ የኮምፒተር ካርታ አሰራር (GIS) ከአቋቋሙት ሙያተኞች አንዱ ነው። የስያትል እና የፖርትላንድ ከተማ የሚገለገሉበት የውሃ ማሰራጫና ማከማቻ ሲስተሞች በአደጋ ቢቋረጡ መከላከሊያ መመሪያ ኦፕሬሽኖች የሆኑ እሱ በአቀደው መሰረት ተቋቁመዋል።

ዘውገ ፋንታ በዚሁ ሙያው በግል ስራ ተሰማርቶ ይገኛል።

Zewge Fanta may be reached by E-mail: zegfantam@aol.com


# I FOUND OUR FLAG

While driving in the city you might have seen many flags around town. You might recognize some of the flags to which country they belong and sometimes you might want to play the guessing game and try to figure out. . What if you see your own flag flying high on the side of the road in front of residential area! I was in Ottawa in the month of July/ 2009. The day was Sunday. I was looking for Ethiopian orthodox church. I made a wrong turn near the church; after driving a couple of hundreds of meter i saw Ethiopian our own flag. First, i thought i found the church. As i got closer, i knew i was wrong since i remember as i was told, the church actually is a big church and it does not look like a residential house. I pulled over and staring at it. Since i was in Ottawa, My first guess was it should be the ambassador resident. I was right.

It feels great, i felt and flew in memories of home. It reminds me my childhood, the place where i played ball, where i went to school and my friends. All it took was the flag by the side of the road in front of the house. This photo on the flag would tell that is the land of Ethiopians. I felt great and was proud to see our flag. Ambassadors' might come and go, but the flag will always fly high reminding everyone that this is part of Ethiopian. I felt i was home for that moment......

**Benyam Woldeab**
**Photographer**



## NEW YORK LIBRARY ASSOCIATION (NYLA) ANNUAL CONFERENCE
## NIAGARA FALLS, NY - OCTOBER 15, 2009

# WILL THE ETHNIC PRESS IN AMERICA SURVIVE?

**Muluken Muchie**
*Editor/Publisher*
*Hawarya News Paper*
*Toronto, Canada)*



**Muluken Muchie(right) with other participants at the NYLA conference**

Greetings, ladies & gentle men;

Before I go further, allow me to start by extending my appreciation to the organizers of the 2009 NYLA conference. I applaud them for their considerate efforts to involve the multicultural media of North America; which have become the eyes and ears of our multicultural society. It is a great privilege for me to attend this conference by representing one of the African multicultural (Ethnic) media called, 'Hawarya', means, "disciple" in Amharic, the Ethiopian official language.

By the way, I like the abbreviation coined to be "NYLA"; it reminds me not only the name of my African antelope species, Nyala, but its characteristics, too.

The Nyala is part of the antelope family found in Africa, particularly in South Africa, as that of the Ethiopian Walia Ibex, which is also belong to the goat family and only its kind found in the Ethiopian northern mountain.

The African Nyala finds its habitat in a dense area of dry savannah woodland or in thick river bank vegetation; it doesn't prefer grass lands or plains as the other common antelopes normally do; but it lives within the savannah or a river bank vegetation where many types of little creatures live side by side. The African Nyalas are known of protecting its vulnerable members, the females and the youths – it is believed up to 30 members of females and youths travel by group to safe guard each other's security and wellbeing. Males of the Nyala species live in solitary of the females and the youths; they only join the herd at favorite feeding and watering places or when there arises natural mating needs; the strong members are not allowed to influence the day to day livehood of the weak. Doesn't this characteristic resemble to an independent institutions as that of NYLA in regard to its members?

I think NYLA is some what similar to that of the African Nyala; It lives within the population where minority groups are struggling to meet ends; it understands the problems and interests of these multicultural groups; it reaches them to help co-exist and grow; that is how and why I am here representing the African Ethnic media by being supported by NYLA.

Ladies & gentle men,

Let me introduce you our news paper, it is called Hawarya; it is a publication in the Ethiopian Diaspora since 1995.

Hawarya is an "Amharic" monthly (Ethiopian official language) published in Toronto Canada. It is the main source of information for its readers, both at home, abroad and for main stream media groups. Hawarya has subscribers all over the world and we also distribute to major North America cities. It has prominent writers and contributors from back home to the Diaspora and it is an active member of the **National Ethnic Press and Media Council of Canada.**

Hawarya's main objectives, in a country (Canada) where multiculturalism is maintained and protected by law, can be sum up at least in three levels:

**1) To keep in touch with our country of origin**

• once we left our country , there is no way to know more about the situation in back home;

• the main stream media report only on **crisis and major events on the international level**, but the community needs to follow every aspects of social, economic and political developments and happenings of the country of origin.

• to meet this strong desire, we had to have an out let that could connect us and learn more about our home country

• so is the reason in part for Hawarya and other ethnic papers to be born - to have the opportunity to exchange news from back home and abroad within the Diaspora community.

**2) To be a bridge between the community and the rest of the society we live in;**

• as new comers and settlers we need to interpret and understand the **Canadian values and system** using our way of understanding;

• for this we need a medium which is useful for information exchanges among the community members themselves concerning vital interests, such as cultural and social events, migration and employment matters..

**3.1) To preserve ones identity**

• **Cultural heritage**
• language
• literature
• history
• values & ways of life

**3.2) To gain strength**
• Economic
• Political
• Social

**Challenges:**

1) the internet factor:

• while it has an advantage to collect and disseminate news and information in a timely efficient way, ethnic media lacks the resource to equip itself with the necessary tools of the net. The internet needs trained staff members in different capacity. When ethnic media lacks to update itself to the technology, readers switch to individual capacities and personalities who disseminate on the net different news items and chatting; this creates a worthiness question.

• Advertisers switch to the internet; create their own websites, use individual netters to promote their products & services

2) the youth factor:

• language barrier to read ethnic papers published in native languages

• although there is a burning feeling to maintain ones heritage, the youths dominantly influenced by the main stream culture where they live in; there is a need to have multicultural institutions that can educate native cultures to youths; this in turn help ethnic media continue serve the community.

Given all of these, the question is, **Will the Ethnic Press in N. America Survive?**

**I believe, yes, it will! Ethnic press will survive in North America.**

**what it has to do is:**

a) keep a strong link with the mother culture, the country of origin; this is an artery, a blood vessel to ethnic media.

b) update the standard of ethnic media to the internet; readers always want to follow an organized and reliable source of information.

c) create institutions that can educate the youths of their culture, language and history; make sure the youths can read and write their heritage languages.

d) help the community grow and be self sufficient to take care of the course of its heritage.

Ladies and Gentlemen:

Hawarya has come a long way in serving its designated community; it has been cited as a reliable source by renowned North American media such as The Globe & Mail, The New York Times, the Toronto Star, CBC local and international, as well as many local publications & air media from within Ethiopia and abroad. Hawarya is one of the symbols of the Canadian mosaic – a society in which multiculturalism is celebrated.

As an editor and publisher, I was profiled by the Toronto Star and York University Magazine.

Thanks and God bless our societies!

TANA
TANA PRINTING ENT.
ጣና ማተሚያ ቤት
ማንኛውንም የህትመት አገልግሎት በየትኛውም ቋንቋ እንሰጣለን።
Complete Printing & Copy Services Including Wedding Invitations

| 2,500 Full Color Business Cards (Both Sides) $125 | 5,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $199 | 10,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $375 |
|---|---|---|

**Limited time offer**
633 Vaughan Rd. Toronto ON. M6C 2R4 (Vaughan & Oakwood)
Tel: 416.654.2020
**Fax: 416.653.6191**
e-mail: print@tanaprinting.com
website: tanaprinting.com

# ህጻንም እንደ ሸቀጥ ???

በዚህ አስቸጋሪ አሳፋሪና የመጥፎ ድርጊት ማስፈፀሚያ መረማመጃ ዘመን ላይ በህይወት በመኖር ከመታዘብ አለማለፋችን አልበቃ ብሎ ትውልድ ማስተላለፊያው ድልድይ ላይ ከነዚህ ሙሉ የህሊናና የአካል ጉዳት ጋር እየተሟገትንለመጭውትውልድ ምንድነው የምናስተላልፈው? በራሱ የሚኮራ ቀጣይነት ያለው ትውልድስ እንደት ነው የምናፈራው ? ተተኪውስ እኛ ያሳለፍነውን መከራ ሳይቀበል እፎይ ብሎ የሚኖረው እንደት ነው? የሚሉትንና መሰል መልስ አልባ ጥያቄዎችን ሳስባቸው በዚህ ትውልድ ላይ የደረሰውንና እየደረሰ ያለው ክምር ችግር የፈጠረው ወይስ.........? እ ር ግ ማ ን ? ለምን ተነጋግረን ላንደማመጥ፡ ተደማምጠን ላንግባባ፡ ተግባብተን ላናብር፡ ተደጋግፈን ላንተዛዘን፡ ተረዳድተን ላንጠነክር፡ ላለመተያየትእንድንለያይሆንን? እልና የጥያቄዎቹ ክምር አንድም በጎ ቃል ላይተፋ የጥያቄ ካብ ብቻ ይሆናል ታዲያ ምናልባት ምናልባት እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም ከረሀብተኛነት እኩል የምንታወቅበት በግል ሮጦ ማምለጥን ነውና ( ጠላቶቻችንም ካበርን ስለምናስፈራቸው በጣም የሚያዳንቁት ይህንን በግል የመጣና የሚመጣን ጉዳይ ነውና ይህም ገና ለምን እንደሚጠቅም በሃገረ ኢትዮጵያዊ ባህላዊ ስነዓዕምሮ ጠበብት ሊጠና ይገባዋል) ይሁንና ለዛሬው ይህን ልዩ ተሰጥኦ መልካምነትን መሰረት ባደረገ ዓላማውን ወደ ሰብዓዊ ጉዳይ ለውጠነው ሁላችንም እሽቅድድም ብንጀምር የጋራ አሸናፊነትን ለመቀዳጀት በመቀጠልም የደረሰብን ሃዘን ከግል ወደ ጋራ ተለውጦ የህብረት ጉዞን ቢያስጀምር በሚል በዚህ ሰብዓዊ ርዕስ ዙሪያ የጋራ እሽቅድድም የሚውልድ ውይይት ለመክፈት ወድጃለሁ

ምናልባት ዋናው ነጥቤን ከጽሁፉ ለመረዳት አጀማመሬ ዝንፍንፍ ቢልባችሁ በስተመጨረሻ ይቃናልና በጎ የንባብ ልቦና ይችራችሁ

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ስለ “ባሪያው ዘመን ንግድ“ ለመተረክ አይደለም ይልቁንም በዚህ ዙሪያ በቂ ዕውቀትና ጥናት የተቸሩ በርካታ እንደሆኑ በቅጡ እረዳለሁ ግን ለዋናው ርዕሴ መንደርደሪያ ወይንም የፊት በር ይሆነኛል ከሚል እንጂ

ልብ በሉ ይህ ንግድ የተጀመረው ከ 400 ዓመት በፊት እንደሆነ ሲጠቀስ ውድ የአፍሪካን ልጆች አፍኖ መሸጡ የተስፋፋው በሃገር አሜሪካ አውሮፓውያን ሰፍረው በያዙት ሰፋፊ መሬት ላይ በወቅቱ ከፍተኛ ትርፍ የሚያመጡትን ትንባሆ፡ ጥጥ፡ የሸንኮር አገዳን እና የመሳሰሉትን በስፋት በማብቀል ይደረግ ለነበረው የትርፍ ሩጫ ከፍተኛ የሰው ሃይል በማስፈለጉ በፖርቱጋሎችና በስፔኖች የተጀመረ በኋላም በእንግሊዞች ሞኖፖል የተደረገ ሰብዓዊነት የጎደለው ንግድ ነበር ታዲያ በዚያን ዘመን “የባሪያ ንግድ“ ጉልበት ያለውን ወንድ ብቻ ሳይሆን ሽያጩ ያተኮረው ሴቶችንም በእኩል የሚያካትት ነበር ሴቶች ከጉልበት ስራው ባሻገር ሌላ ባሪያ እንዲወልዱ ይጠበቅባቸውም ነበር ለዚሁም ዕድሜያቸው 13 እና 14 ሲደርስ አግብተው መውለድ እንዲጀምሩ ሲደረግ በዚያውም ፍጥነት በያመቱ አንድ አንድ ልጅ መውለድም ዋንኛው ተግባራቸውና ግዴታም ጭምር ነበር የተወለዱትም ልጆች እድሜያቸው ተገቢ ዕድሜ ተበሎ የተመደበለት ላይ ሲደርስ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለሽያጭ አለበለዚያም ወደዚህ ዓለም የተላኩበትን የባርነት ውርሳቸውን ይያያዙታል!

ታዲያ ይህ ዘግናኝ ወቅት ጥሎ የሄደው ጠባሳ ወገኖቻችንን ለባዕዳን በትንንሽ ጥቅማ ጥቅም አሳልፈው ይሸጡዋቸውና ይለውጧቸው የነበሩት የራሳችን ወገኖች አፍሪካውያን ነበሩ:: ይህ የተመዘገበልን አሳፋሪ ታሪካችን ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ እየመጣ ተሸጠው በነበሩ አፍሪካውያን ትውልድና ሲሸጡ በነበሩ አፍሪካውያን ትውልድ ዙሪያ ቂም በቋጠረ ወቃሽና ጸጸት ባዘለና አንገት በሰበረ ትውልድ መሃከል መድሀኒት ያጣ ፍጥጫ ዛሬም ሲዘከር አለ::

ታዲያ በዚያ አስከፊም ዘመን የተሻለ “ባሪያና“ የተከፋ “ባሪያም“ ተከፋፍሎ ይኖር ነበር:: የቤት ውስጥ “ባሪያ“ ከሜዳ ላይ “ባሪያ“ እራሱን የተሻለ ያደርጋል:: በዚያንም ወቅት በዚያ ግፍ መሃል ከፍተኛ የጋራ ግንዛቤ ክፍተት ነበረ:: በመሆኑም ይህ የግንዛቤ ክፍተት የነጻነት ትግሉን ክፉኛ ከጎዳውም ሆነ ከጎተተው በዋናነት ይጠቀሣል:: የነጻነት ታጋዩን የፈተነውም ይህው የግንዛቤ ልዩነት ነበር:: በመሆኑም የነጻነት ታጋዮች ከባርነት እንዴት ነጻ መውጣት ላይ ከሚያጥፉት ጊዜ በባርነት ወጥመድ ያለውንና የተሻለ በመኖሩ ግንዛቤው የተተንሸዋረረውን በመመለሱ ላይ ነበር::

ዛሬ ይህ የባሪያ ንግድ በዓለማችን በየትኛውም ሃገር በህግ የመከልከሉን ያህል መልኩንና ቅርጹን እጅግ ለውጦና “በዘመናዊነት“ ራሱን “አሰልጥኖ“ በአመለካከት ትልቅ የግንዛቤ ሸውራራንትን በማስረጽ ይኸው እንደገና በይበልጥም በኢትዮጵያውያን ላይ አሳፋሪና ለትውልድ አንገት አስደፊ ታሪኩን ሊጽፍልን ሲንደረድር እያየን ነው:: አዎ አሳፋሪ የሃፍረት ታሪክ!!! ሃገራችን ኢትዮጵያ ህጻናትን በመሸጥ ከአለማችን ክብረወሰኑን ለመውሰድ በከፍተኛ ፍጥነት ላይ ትገኛለች::

የዚህ ጽሁፍ አላማ ይህንን “የሰለጠነ የህጻናት ንግድ“ በተመለከት በሁላችንም መሃል አንድ ዓይነት ግንዛቤ ሊፈአጥር ይችላል ከሚል ቅዥት ወይንም የሃዘን እንጉርጉሮ ለመደርደርም አይደለም:: ከግንዛቤ መዛባት በመከራከሪያነት ለሚቀርቡት ነጥቦች ንፅፅራዊነት ይረዳል ከሚል እሳቤ እንጂ::

ከሁሉም በቀዳሚነት ግን በዚህ ጉዳይ ዙሪያም ሆነ በተለያዩ የሃገራችን ጉዳዮች ላይ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እየሰጠ ላላው አንድና አንድ የፖለቲካ ድርጅት ኢህአፓ ከፍተኛ አክብሮቴን እያቀረብኩኝ አንባቢያን በዚህ ዙሪያም ቢሆን ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጠንካራ ተመሳሳይ አቋማቸውን ተመልክታችሁ ከሆነ (እኔ ስላልተመለከትኩ ነውና) ካለ ግን እኩሌታ አከብሮቴ ይቸርልኝ እላለሁ::

ሆኖም ግን ቅደመ ማስጠንቀቂያውም ሆነ ዘግናኝ የሆንው በሃገራችንም ሆነ በህዝቧ ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ ከሰሞነኛ መፎከሪያነት ወይንም መታያነት አልፎ መሪ ድርጅቶችን በመደገፍ ተባብረን ችግሩን ለመቅረፍ ወይንም የባሰ ጥፋትእንዳይፈጠርበቁርጠኛነት ስንታገል አለመታየቱ የትግራይ ነጻ አውጭ ነኝ ለሚለው ቡድን ከፍተኛ የልብ ልብ ቸሮታል ቢባል ሙግት የሚገባ አንደበት እንደማይፈጠር ግን እርግጠኛ ነኝ::

አዎ አሳፋሪ ዘግናኝ የህጻናት ንግድ ከባሪያው ዘመን ንግድ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በአንጻራዊንት እንመልከትው:: በመጀመሪያ ግን ልዩነቱን

-- “በባሪያው ንግድ ዘመን“ ይሸጡ የነበሩት ነፍስ ያወቁ አቅማቸው ቢያንስ ለስራ የደረሱትን ሲሆን በህጻናት ንግዱ ግን ነፍስ የማይውቁ ጡት ጠብተው ያልጠገቡትን ህጻናት ነው

---”በባሪያው ንግድ“ ዘመን እነዚያ የቀድሞ ወገኖቻችን የሚኖሩት ተሰባስበው አንድ አይነት ባህል ቋንቋ እና ቀልም ያላቸው መጋባትና መውለድ የቻሉ ቢያንስ ጌቶቻቸውን “ማማት“ የቻሉ ሲሆኑ በዚህ የህጻናት ንግድ ጡት ጠብቶ ያልጨረሰን ህጻን እንዲህ ብሎ ለማነጻጸር ለአንባቢያን ተራውን ልተው

----በባሪያው ዘመን ንግዱ አላማው የታወቀ ነበር- ይሀውም ጉልበት:: አዎ ግፈኛ የሆነ ነጻ የሆነ ክቡር የሰው ልጅ እንደሰው ያልታየበት ነጻ ጉልበት በዚህ በህጻናት ንግዱ ላይ የንግዱ አላማ ይህ ነው ተብሎ ለመግለጽ እያንዳንዱን ህጻን በገዛ ጌታ የሚወሰን ነው:: ነገር ግን የዚህ ጽሁፍ ለግንዛቤነት አንዱን ብቻ ለማቅረብ ይሞክራል:: ባልፈው ሰሞን በፈረንሳይ ሃገር በሁለት ህጻናት ላይ የደረሰውን እጅግ ሰቅጣጭ ሰሞነኛ ዜና በአሜሪካኑ የአማርኛ ክፍለጊዜ ለተከታተለ (በጽሁፍ ለማቅረብ እጅግ ዘግናኝ ነውና አላቀርበውም) ተመሳሳይ ወይንም (ምን ከዚህ በላይ ሊኖር እንደሚችል ባላውቅም ሊኖር ይችላል) የከፋ አላማ እንዳለው ይታመናል:: ነገር ግን ይህ የንግድ ዘርፍ ራሱን እጅግ አሰልጥኖ “ዘመናዊነቱ“ ከፍተኛ የግንዛቤ መዛባትን እንደ “ባሪያው“ ዘመን ጊዜ ፈጥሮአል::

ከልዩነቶቹ በጥቂቱ ይህንን ካልን አንድነቱ ግን በጣም ግልጽ ነው:: የሰው ልጅ ባላመነበት ባልፈለገው በማይፈቅደው ሁኔታ በግዴታ በአፈና ተሸጦ እንደ እራሱ ሳይሆን እኩል በተፈጠረባት ምድር ላይ እጅግ በተዛባ መልኩ እንደ ሌሎች ፍላጎት እንዲኖር መደረጉ ነው:: ለሰበአዊ ፍጡር ከፍተኛ ክብር አለው በሚባልበት በዚህ “የሰለጠነ“ ዘመን “በሰለጠኑ“ ሃገሮች ህጻናት ይሸጣሉ!

ህጻናቱን ለመሸጥ ከሚሰጡት ዋንኛ ምክንያቶች አንዳንዱን በማንሳት የምክንያቶችን አሳማኝነት እንመርምር:

1- የሚበላ ያጡ አሳዳጊ የሌላቸውን የወደፊት ተስፋ መስጠት የሚል ነጥብ ሲቀርብ በዚህ መከራከሪያ ዙሪያ የተፋጠጠ ነገር ውስጥ ከመግባቴ በፊት የትግራይ ነጻ አውጭዎች ለባእዳን ምጽዋት ይረዳቸው ዘንድ “ህውዜን“ የተሰኘውን ዘግናኝ ትርኢት “ወገናችን እና ዘራችን“ በሚሉት ወገናችን ላይ እንዴት እንዳቀናበሩት ከራሳቸው ውስጥ አዋቂ ላዳመጠ (አቶ ገብረ መድህንን ይጠቅሳል) እንኳን አንድ የኔ የማይሉት ወገኔ የማይሉት ህጻን ይህንን ያህል ዋጋ ማውጣቱን አውቀው ለንግዳቸው መስፋፋት የማይፈነቅሉት ምክንያት አለ ለማለት ቢያስቸግርም እንደ ህዝብና ሀገር ይህንን የመዋጋት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያኖች ግዴታም ሲሆን እንኚህ ህጻናት በተፈጥሮ የትውልድ መብታቸው በትግራይ ነጻ አውጭ ለትርፍ ሊሸጡ ሳይሆን የትግራይ ነጻ አውጭዎች ከተቀራመቱት ኢትዮጵያዊ የተፈጥሮ ሃብት ሊካፈሉ ድርሻቸው እንጂ::

እንግዲህ ይህ የንግድ ትርፍ በአንድ ህጻን ከ$23000 እስከ $25000(ከሃያ ሶስት ሽህ እስከ ሃያ አምስት ሽህ ዶላር) የሚያስገኝ ነውና በምክንያትነት የሚደረድሩት አዳኝነታቸውን ከፍተኛ ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል:: ለግንዛቤ ያህል የተራበ መዳን ያለበት ህጻን ለምን መሸጥ አስፈለገው? ይህንንስ የሽያጭና የግዥ ልውውጥ ከሰብዓዊ ቸርነት ጋር እንዴት ባለ መልኩ ነው ማስታረቅ የሚቻለው? ግዢ ማለተስ የባለቤትነት ማረጋገጫ ዋስትና አይደለም ወይ? አንድ ህጻን ለመርዳትስ ለሁለተኛና ሶስተኛ ደላላ ክፍያን ምን አመጣው? ህጻናትስ ሲሆን ከወላጆቻቸው ካልሆነም በደረጃ ከሚቀርቧቸው ቤተሰቦች ጋር የመኖር ተፈጥሮአዊ መብታቸው አይደለም ወይ? ሰው ሰራሽ (በአብዛኛው) በሆነ ችጋር ቤተሰብን አጣብቂኝ ውስጥ በመክተት ህጻናትን የሚመነትፍ ሱቅና ሰራተኛን ምን አመጣው? እናም እናም ብለን ለመልስነት የሚያስቸግሩ ጥያቄዎችን መድርደር ይቻላል:: የነዚህ ጥያቄዎች መልስ በትግራይ ነጻ አውጭዎች ለሚነሱት ምክንያቶች በቂ መልስ ይሰጣልና:: ይህ አይን ያወጣ ዝርፊያ ወፈፌ ሰኞና ሰኔ የገጠሙበት ዘመን ነውና ሁሉም ፈዞ ንግዱም ጦዞ ለቁጥር የሚያዳግቱ ህጻናት በዚሁ የትግራይ ነጻ አውጭ ተሸጠው ካገር ወጥተዋል::

ይህ በትውልድ የባንዳነት ታሪክ በበታችነት ስሜት የተወጠረ የትግራይ ነጻ አውጭ ቡድን በከፍተኛ እልህ ሀገርንና ትውልድን ሲያጠፋ በአንጻራዊንት ሀገርና ወገን መዳን አለበት የሚለው ወገን ላለፉት አስራ ስምንት አመታት በጠራራ ጸሀይ የሚፈጸሙትን ወንጀሎች በሰሞነኛ ዜናነት መፎከሪያ ከማድረግ በዘለለ (ለዛውም ዜናውንም ለህሊናቸው የቆሙ ባእዳን ሲንግሩን) የሚፈጸመውን ወንጀል ለመግታት ወይንም ቢያንስ ወደከፋ ጥፋት እንዳይዛመት ስንከላከል አይታይም:: እንግዲህ ነገሮች ከረውና መረው የተወሰኑ ዘሮችን በጭፍን ጥላቻ ለማጥፋት እየተገበር ያለው

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

# የክቡር ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ 100ኛ ዓመት ልደት

ከገጽ 15 የዞረ
ይህንንም በሚመለከት:-

2ኛ) እኔ በዓይኔ ያየሁትን አጠር አድርጊ ለመናገር እሞክራለሁ::

1. የታህሳሱ 1953 የመንግሥት ግለበጣ ከከሸፈ በኋላ ክቡር አቶ ሀዲስ ለንጉሡ በድፍረት ያቀረቡትን የአስተዳደር ማሻሻያ ባለ 13 ገጽ ሰነድ በመኖሪያ ቤታቸው በሚገኘው ጽ/ ቤታቸው ውስጥ አስነብበውኛል:: "ታዲያ የዚህ ሰነድ ዕድል ምን ሆነ?" ብዬ ብጠይቃቸው የሚከተለውን መልስ አግኝቻለሁ፤ አጠቅሳ-ለሁ:-

" ጃንሆይ ሰነዱን ካነበቡ በኋላ ጠቅላይ ምኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድን÷ ጄኔራል አቢይ አበበንና እኔን አነጋገሩን:: በሰነዱ ላይ ተመርኩዘን ለሀገርና ለመንግሥት የሚጠቅም የተግባር ዕቅድ እንድናቀርብ በማዘዝ ሰነዱን እፊታችን ላይ ለጠቅላይ ምኒስትሩ ሰጧቸው:: ጄኔራል አበበም÷ ጃንሆይ÷ ይህ ሥራ ከባድ ስለሚሆን ተጨማሪ ሰው ይታዘዝልን በለው ኃሳብ አቀረቡ:: ጃንሆይ ግን ፈቃደኛ አልሆኑም:: ጄኔራል አበበም እንደገና "ባይሆን በፀሐፊነት እንዲረዳን ከተማ ይፍሩ ይመደብልን" ብለው አሳሰቡ:: ጃንሆይም በኃይል ቃል÷ የለም እናንተ ብቻ ትበቃላችሁ በለው አሰናበቱን:: ከዚያ በኋላ ሰነዱ የት እንደገባ ሳይታወቅ ቀረ " ብለው አቶ ሀዲስ መልሰውልኛል::

2. በደርግ ጽ/ ቤት የተደረገ ፍጥጫ፤

አንድ ቀን የደርግ ወታደሮች የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞችን ማኅበራቸው ያሳለፈውን ውሳኔ የያዘ ወረቀት በትናችኋል በማለት ቦሌ አየር ማረፊያ አካባቢ ተኩስ ከፍተው ይገድሏቸዋል:: ብሄራዊ ሸንጎው ግድያውን በመቃወም የውግዘት ውሳኔ የያዘ ደብዳቤ ለደርግ ይልካል:: የሸንጎው ውሳኔ ያስቆጣቸው ደርጎች፤ ዛ ቻ የተላበሰ ደብዳቤ በመንግሥቱ ኃይለማርያም ተፈርሞ ወደ ሸንጎው ይልካሉ:: ሸንጎው በተላከው የደርግ ደብዳቤ ላይ ከተወያየ በኋላ ጥቂት አባላትን የያዘ ልክ ወደ ደርግ ጽ/ ቤት ሄዶ ስለ ጉዳዩ እንዲነጋገር ይወስናል:: በውሳኔው መሠረትም÷ አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ÷ አቶ አሰፋ ሊበን ÷አቶ መንግሥቱ ለማ÷ አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ÷ አቶ በየነ አብዲና ተገኘ ሞገስ ወደ ደርግ ጽ/ ቤት በመሄድ ከመንግሥቱ ኃ/ ማርያምና ሌሎች ሁለት የደርግ አባላት ማለትም ከሻለቃ ፍስሐ ደስታና ከመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ ጋር ይገናኛል:: ሦስቱም ሽጉጥ አገልድመው ወደ አዳረሹ ይገባሉ:: ሁኔታው በፀጥታ ብቻ ሳይሆን÷ በፅልመትም የተሸፈነ ነበር:: የዚህን ፅልመት ጭጋግ የገፈፉት ክቡር አቶ ሀዲስ ነበሩ:: ከተላክነው ሰዎች ውስጥ መጀመሪያ የተነገሩት እርሳቸው ሆኑ:: ጥበብን÷ ማስተዋልን÷ ድፍረትንና ለዘብታን በተላበሰ አነጋገር "ሻለቃ መንግሥቱ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ እኮ በሚገባ አታውቁትም:: በኃይል ለመግዛትም ያስቸግራችኋል:: ሰው መግደሉ ይቆም፤" ብለው ተናገሩ:: መንግሥቱም በበኩሉ÷ " ትላንት የፀጥታ ጠባቂ ወታደሮች የፈፀሙት ድርጊት ሁላችንንም አሳዝኑዋል::" ካለ በኋላ "ቢሆንም እኮ 'አብዮት ልጇን ትበላለች' ይባል የለ እንዴ? " ሲል በትዕቢት የተመላ ምፅት ተናገረ:: ስብሰባውም ያለ አንዳች እልባት አለቀ:: ከሁለት ስዓታት ፍጥጫ በኋላ እኛ ወደ ሸንጎው ተመልሰን ሄደን የሆነውን ሁሉ ለጠቅላላው የሸንጎ ስብሰባ አስረዳን::

ክቡር አቶ ሀዲስ÷ ትክክለኛ ነው ብለው ያመኑበትንና ከህሊና ወቀሳ ነፃ የሚያደርጋቸውን ዓላማና ተግባር÷ እንዲሁም ለሀገር ይጠቅማል የሚሉትን ኃሳብ ሁሉ ያለ አንዳች ስጋትና ያለ እበላ ባይነት ለሀገሪቱ መሪዎች ማቅረብ መተከላዊ መርሆአቸው ስለነበር፤ በዚያ በሚያስፈራው በደናግ ዘመን እንኳ ቢሆን ይህንን ከመፈፀም አልታገዱም::

ክቡር አቶ ሀዲስ ደርግ ይቀበሉ ያላቸውን የጠቅላይ ሚኒትርነቱን ቦታ ለምን እንዳልተቀበሉ ስንጠይቃቸው÷ እንደሚከተለው ነግረውናል:-

" አንድ ቀን ጄኔራል አማን በስልክ ጠራኝና ተገናኘን:: ደርጎቹ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ እንዲይዙልን ጠይቅልን ብለውኛል ብሎ ነገረኝ:: እኔም አስቤ አስውቃለሁ ብየ መለስኩለት:: ለመልሱ እንድነገናኝ በቀጠሮ ተለያይን:: በቀጠሯችን ስንገናኝ÷ መላውን የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የሚወክሉና የሠራዊቱንም ተጠሪዎች የያዘ ጊዚያዊ የመሸጋገሪያ መንግሥት ይቋቋምና በዚህ ሂደት ውስጥ ያቅሜን አስተዋፅዖ አድርጋለሁ:: ከዚያ በፊት ግን ወታደሩ ወደ ጦር ሰፈሩ መመለስ ይኖርበታል:: ብየ መለስኩለት:: በማግስቱ ደርግ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሀዲስ አለማየሁ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ተጠይቀው ፈቃደኛ አልሆኑም የሚል ዜና ሰማሁ:: ጉዳዩ በዚህ አበቃ" ብለው ለኮሚቲያችን መልሰዋል::

የክቡር አቶ ሀዲስን ሰብዕና በትክክል የሚገልጹ ናቸው ብየ የተዘብኳቸውን አንዳንድ በግል ያጫወቱኝን አጋጣሚዎች ልናገር እፈልጋለሁ::

ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ በኢጣሊያ ደሴት ተግዘው በነበሩበት ወቅት ከአጋጠሟቸው የተለያዩ ክስተቶች ውስጥ በርከት ያሉትን ቢነግሩኝም÷እኔ ግን ዛሬ አንዱን ብቻ መርጩ ልናገር እፈልጋለሁ:: ይህም÷ ከፍተኛ የውሀ ዋና ችሎታቸውን የገለፁበት አጋጣሚ ነበር:: በሮማ ዩኒቨርቲ ስትማር የነበረች አንዲት ወጣት ኢጣሊያዊት በበጋ ወራት እናቷን ለመጠየቅና የዕረፍት ጊዜዋን ለማሳለፍ እነ አቶ ሀዲስ ተግዘውበት ወደነበረው ደሴት ትመጣለች:: ከግዞተኞቹ ኢትዮጵያውያን መካከል አንድ ዘመናዊ ትምህርት ከተማሩ ሰው ጋር ጓደኝነት ትመሰርታለች:: ጓደኝነታቸው እየጠነከረ-እየጋለ ይሄዳል:: ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያዊው ግዞተኛና ይህች ወጣት ጣሊያናዊት በበህሩ ዳርቻው ሁልጊዜ ይንሸራሸራሉ:: ይህን ተመለክቶ የቀና አንድ ኢጣሊያዊ ወጣት መኮንን÷ "ከዚህች ልጅ ጋር ሁለተኛ እንዳላይህ÷ እኔ ፍፈልጊያታለሁና:: አሻፈረኝ ካልክ÷ ሁለታችን ይዋጣልን:: ቡጢ እንግጠምና ያሸነፈ የርሷ ጓደኛ ይሆናል" ብሎ ለኢትዮጵያዊው ግዞተኛ የይዋጣልን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል:: ይህንን ጉዳይ እኝህ ግዞተኛ ለጓደኛቸው ለክቡር አቶ ሀዲስ ያዋዩዋቸዋል:: ክብሩ አቶ ሀዲስም በበኩላቸው ለይዋጣልኑ ድንፋታ እንዳይበገሩ ጓደኛቸውን ያበረታታሉ:: ጎደኛቸውም "እኔ ይህን የኢጣሊያ መኮንን በቡጢ አልችለውም " ብለው ስጋታቸውን ይገልጹላቸዋል:: አቶ ሀዲስም÷ "በቡጢ ሳይሆን በውሃ ዋና እንጋጠም ብለህ ጠይቀው::" ይሏቸዋል:: ጓደኛቸውም "ወሃ ዋናውንም እኮ አልችልበትም:: " ብለው ይመልሱላቸዋል:: ክቡር አቶ ሀዲስም "ግዴለም÷ ብቻ ጣሊያኑ በውሀ ዋና ውድድር ይስማማ እንጅ እኔ ስለአንተ ሆኘ እግጥመውና አሸንፌዋለሁ:: " ይሏቸዋል:: ጓደኛቸውም "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ጉዳዩ የኔ ነው:: እኔኑ እኮነው ጣሊያኑ ይዋጣልን ያለኝ:: " አሏቸው:: እንግዲህ ያቶ ሀዲስ አለማየሁ የተራቀቀ ዘዴ የሚታየው እዚህ ላይ ነው፤ "አንተ ራስክን በኢትዮጵያ ውስጥ ሳለህ የሀገሪቱ የውሀ ዋና ሻምቢዮን እንደነበርክ ግለጽለትና ጣሊያኑ ከአንተ ከኢትዮጵያዊው ሻምፒዮን ጋር ከመወዳደሩ በፊት÷ ከሀዲስ ጋር ተወዳደርና ሀዲስን ካሸነፍክ ከኔ ጋር ትገጥማለህ ብለህ በለው " ይሏቸዋል:: ጣሊያኑ በዚህ ይስማማል::የውድድሩ ቀን አንድ እሁድ ከስዓት በኋላ እንዲሆን ይወሰናል:: ኢትዮጵያውያን ግዞተኞች÷ የልጅቷ ቤተሰቦችና የአካባቢው ነዋሪ ወደ ባህሩ ዳርቻ ውድድሩን እንዲመለከት ይጋበዛል:: የውድድሩ ርቀት በባህሩ ውስጥ በብቸኝነት የቆመችውን ቋጥኝ ነክቶ መመለስ እንዲሆን ይወሰናል:: የውድድሩ ዳኛ÷ "ኡኖ! ዱዌ! ትሬ ብሎ ከቆጠረ በኋላ የያዘውን የስፖርት ሽጉጥ ተኩሶ የዋናውን ውድድር እንዲጀምሩ÷ የኢጣሊያኑን መኮንንና አቶ ሀዲስን ይለቅቃቸዋል:: ክቡር አቶ ሀዲስ በማይታመን ፍጥነት ቋጥኟን ነክተው በመመልስ ተወዳደሪያቸውን በማሸነፍ÷ ለጓደኛቸው ሚች ብቻ ሳይሆኑ÷ የግዞተኞችንም ክብር አስረግጠዋል:: አባሾቹ ግዘተኞችም÷ "ብር አምባር ሰበረልሽ÷ ኢትዮጵያ ልጅሽ" እያሉ ወደ የክፍላቸው ገቡ:: ብለው ነግረውኛል::

ክቡበር አቶ ሀዲስ ፈጥኖ የማሰብና ወዲያውኑ ትክክለኛ ውሳኔና መልስ መስጠት የሚችል ፈጣንና ብሩህ እዕምሮ የነበራቸው ሰው ነበሩ:: አንድ ቀን በፓርላማው ውስጥ በሚገኘው ካፌቴሪያ ውስጥ ሁለታችን ቡና እየጠጠን እያለን÷ ተቀናጠሁ ብዬና÷ አቅሜንም ሳላውቅ ምናልባትም÷ " የቄስ ሚስት አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሃፍ አጠበች::" እንደሚባለው ተረት ሆኖብኝ ነው መስል÷ በአንድ ነገር ተተናኮልኳቸው÷ እንዲሁም አልኳቸው:-

" ጌታዬ÷ አንድ የጎጃም ጎረምሳ ፍቅረኛውን ምን እንዳላት ሰምተዋል?"
አልኳቸው:: "ምን አላት?" አሉኝ::

"ጎጃሜ ቡዳ ነው ብለሽ አውርተሻል÷
ሰውን ሰው ሲበላው የት አባሽ አይተሻል?"
ብሎ አላት ብየ ስላቸው÷
ከመቅጽበት የሚከተለውን መልስ ሰጡኝ፤

" እንዴ? ታዲያ÷ ቡዳ ነው ቢሉትም ጎጃሜውን ሁላ÷
ጓቅር የት ይገኛል ሰው አንጀት ካልበላ÷ ብሎ አይጨምርበትም ነበር ? "
ብለው ፈጣን መልስ ሰጡኝ:: እኔም አፌን በዳቦ ብየ ቀረሁ::

የክቡር አቶ ሀዲስን ሰብዕና የተለየ ክብርና ሞገስ ከሚያስለግሳቸው መካከል አንዱ ÷ስለ ጋብቻ ቅዱስነት÷ ስለ ዕውነተኛ ፍቅርና÷ ስለ ትዳር ክብር የነበራቸው ፅኑ ዕምነትና ያሳለፉት እንከን የሌለው ህይወት ነበር:: በግል እንዳጫወቱኝ÷ ክቡርነታቸው ለፍቅር ያላቸው ዕምነት÷ ማለትም÷ "ፍቅርን" የሚያዩት "እስከ መቃብር" ድረስ ብቻ ሳይሆን ÷ ከመቀብርም ባሻገር ተራምዶ በማለፍ÷ የሙታንን ዓለም ዘልቆ በሄደ ትዝታም ጭምር ይመስለኛል:: ለክቡርነታቸው ጋብቻና ፍቅር ለህይወታቸው አልፋና ኦሜጋ እንደ ነበረ በህይወታቸው ዘመን ሁሉ አስመስክረዋል:: ለክቡርነታቸው÷ የመጀመሪያም የመጨረሻም ለሆነው ጋብቻቸው የተለየ ክብርና ፍቅ ስለነበራቸው ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ ክበበ ፀሐይ ከሞቱባቸው በኋላ ትዳር አልመሰረቱም:: እንዲያውም የመኖሪያ ቤታቸውን ለባለቤታቸው ማስታዎሻ ይሆን ዘንድ በስማቸው የሚጠራ የመዋዕለ-ሕፃናት ተቋም እንዲሆን ለአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ከአስረከቡ በኋላ÷ እስከ ዕለት ሞታቸው ድረስ ቃልኪ-ዳናቸውን አክብረውና ጠብቀው ኖረዋል:: .

ክቡር ሀዲስ ዓለማየሁ÷ ለእኔም÷ በመርህ ላይ የተመሠረተ ህይወትና ባህሪ እንዲኖረኝ የሚያስችለኝን ምክር ሰጥተውኛል:: እንዲህም በማለት መክረውኛል:: እጠቅሳለሁ:-

"ተገኘ÷ በነባቢትም ሆነ በድርጊት የምትፈፅማቸውን ሁሉ÷ ሰው ይወደኛል ወይም የጠላኛል ብለህ አታድርግ:: ሰው ይወደኛል ብለህ የምታደርግ ከሆነ÷ ምናልባት ለጥቅምና ለመወደድ ብለህ ሊሆን ይችላል:: ይህን ካደረግህ እበላ ባይነትን ልታነፀባርቅ ትችላለህ:: በአንፃሩ ደግሞ ሰውን በመጥላት ስትልም አንዳች ተግባር አትፈጽም:: በጥላቻ ላይ የተመሰረተ አድራጎት ምናልባት ሳታውቀው ወደ በቀል ርምጃ ያመራህ ይሆናል:: ምንም ጊዜም መፈጸም ያለብህ ከኅሌናህ ወቀሳ ነፃ የሚያደርግህን ብቻ መሆን አለበት:: ሁል ጊዜ ለኅሌናህ ብቻ ተገዥ ሁን:: " ሲሉ መክረውኛል::

በሃያኛው ምተ-ዓመት ውስጥ በነበረችው ኢትዮጵያ ሀገራችን አንፀባራቂ የታሪክ ምዕራፍ አስመዝግበው ያለፉትን የክቡር ሀዲስ አለማየሁን መቶኛ ዓመት የልደት ቀን ለማክበር በተዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ ይችን አጭር ምስክርነት ለመስጠት ዕድሉን ስላገኘሁ÷ የሲፖዚየሙን አዘገጆች በድጋሜ አመሰገናለሁ:: ኢትዮጵያ ሀገራችንም በዚህ በያዝነው ሃያ አንደኛው ክፍል ዘመን አያሌ ሀዲስ ዓለማየሆችን እንድታፈራ እምኝላታለሁ::

አመሰግናሉ!

ተገኘ ሞገስ
ጥቅምት 2002 ዓ.ም
ዋሽንግቶን ዲሰ

# የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በአዋጅ ለመለወጥ የሚደረገውን በመቃወም በቶሮንቶ፤ ካናዳ የቅንጅት /መኢአድ ድጋፍ ድርጅት ፐቲሽን ማስፈረም ጀመረ






በወያኔ ኢሕአዴግ ፓርላማ ለብዙ ሺህ አመታት የኢትዮጵያና የሕዝብዋ መለያ ሆነ የቆየችውን የኢትዮጵያኝ ስንድቅ ዓላማ በአዋጅ ቁጥር 654/2001 ለመለውጥ መወሰኑን በመቃወም በአገር ቤት መጠነ ሰፊ የሆነ የተቃውሞ ድምጽ መኢአድ ከሕዝብ ጋር ሆኖ አያሰማ መሆኑን በዜና ማሰራጫዎች ተሰምቷል።

የመኢአድ ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልም በተደጋጋሚ በዜና አውታሮች በሰንደቅ ዓላማ መለወጥ ጉዳይ ላይ ቃለ መጠይቅ ማድረጋቸው፣ መኢአድም የተቃውሞ መግለጫ ማውጣቱንና ሕዝባዊ ስብሰባ በማድረግ የተቃውሞ ድምጽ አያሰማና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመክርና ሳይወስን ማንም መለወጥ አይችልም በማለት ወቅታዊና ሕዝባዊ አጀንዳ ይዞ በመታገል ላይ ይገኛል።

በዚሁም መሰረት በካናዳ የቅንጅት መኢአድ ድጋፍ ድርጅት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማን ለመቀየር የሚደረገውን በመቃወም በቶሮንቶ ከተማ ኢትዮጵያውያን የ2002 አዲስ ዓመት በዓልን ለማክበር በሚገኙበት ቦታ በመገኘት ጉዳዩን ለሕዝብ በማሳወቅ የፊርማ ማሰባስብ ሥራ መጀመሩንና በእለቱ በርካታ ኢትዮጵያውያን ድጋፋቸውን በማሳየት የተቃውሞ ፐቲሽን ላይ ስምና ፊርማቸውን አኑረዋል።

ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶርንቶ (በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ድርጅት ) በዚህ የታቃውሞ ፊርማ ማሰባሰብ ሥራ በመጀመሪያው ቀን በጣም የተሳካና አጥጋቢ መልስ ያገኘ ሲሆን የፊርማ ማሰባሰቡ ተግባር የሚቀጥል መሆኑ ታውቋል።

የቶሮንቶው የድጋፍ ድርጅት ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሕዝቡን ለመድረስና ለማግኘት በአጭር ቀናጥ ውስጥ የወሰነ ሲሆን የአዘጋጁ ክፍል ከሕዝቡ ባገኘው በጎ ምላሽ ተበራትቶ አስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል ድረስ ሲያስፈርሙ ቆይተዋል።

የድጋፍ ድርጅቱ ስምና ዓርማ በድንኳኑ መግቢያ ላይ ተሰቅሎ በኢትዮጵያና በካናዳ ስንደቅ ዓላማ አሸብርቆ፣ የተቃውሞ ፊርማ በአንድ በኩል አየተካሄደ ከጎኑ ደግሞ ቡናው ከነቁርሱ ቀርቦ አጣኑ ጨስ ጨስ አያለ ዓመት በዓሉን ሲያስታውስ በባሕል ልብስ ያሸበረቁት አህቶቻችን ሕዝቡን ሲያስተናግዱ፡ ሕጻናት ደግሞ አንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ የሚል የኢትዮጵያ ስንደቅ ዓላማ ያለበትና በቀለም ያሳመሩት የአንቁጣጣሽ አበባ ስአል ደግሞ የድሮውን የአገር ቤት ትዝታን ቀስቅሷል።

የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ድርጅት በዚህ ዝግጅት ላይ የተሳተፉትን፣ ወደ ድንክዋኑ በመምጣት ስምና ፊርማችውን ያኖሩትን ሁሉ አያመሰገነ፤ የ2002 ዓዲስ ዓመት የሰላማና የደስታ የድል ዘመን አንዲሆን በመመኘት ሁሉም ለሀገሩ፣ ሊትዮጵያ ሕዝብና ለስንደቅ ዓላማው በአንድነትና በጋራ አንዲቆምና አንዲታገል ያሳስባል።

በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ
ድጋፍ ድርጅት
ቶሮንቶ
መስከረም 2 ቀን 2002










# የኦንታሪዮ ጠቅላይ ገዥ ክቡር ዳልተን ማክጊንቲ (Hon. Dalton McGuinty) ለማህበረሰባዊ የብዙሃን መገናኛዎች ገለጻ አደረጉ!



ክቡር ዳልተን ማክጊንቲ ለኮሚኒቲ የብዙሃን መገናኛ አባላት ገለጻ ሲያደርጉ፤ ፎቶ በሐዋርያ የተወሰደ

የካናዳ ብሄራዊ ማህበረሰብ ህትመትና የብዙሃን መገናኛ ምክር ቤት (NATIONAL ETHNIC PRESS AND MEDIA COUNCIL OF CANADA) ባደረገላቸው ግብዣ መሠረት የኦንታሪዮ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪና መሪ ክቡር ዳልተን ማክጊንቲ በምክር ቤቱ ወርሃዊ መደበኛ ስብሰባ ላይ በኩዊንስ ፓርክ አስተዳደራዊ ጽ/ቤት ተገኝተው ገለጻ ማድረጋቸውን ከቦታው ተገኝተን ዘግበናል።

ክቡር ዳልተን ማክጊንቲ የማህበረሰብ መገናኛ አውታሮች ሰፊ ለሆነው የህብረተሰብ ክፍል እየሰጡ ያሉለውን አገልግሎት እንደሚያደንቁ እስገንዝበዋል። በተለያዩ ባህሎችና ቋንቋዎች ለተገነባችው ካናዳ መሠረታቸውን ማህበረሰባቸው ያደረጉ የብዙሃን መገናኛዎች ትልቅ አገልግሎት ሊሰጧት እንደሚችሉ ጠቅሰዋል። ካናዳ እንደ ቻይና፥ ህንድና ከመሳሰሉት ሀገሮች ጋር ለምታደርገው የ ንግድና የውጭ ግንኙነት በውስጧ ባሉ ዜጎቿ እየተዘጋጁ አገልግሎት የሚሰጡ ማህበረሰብዊ የብዙሃን መገናኛዎች እጅግ ጠቃሚ መሆናቸውን ትኩረት ሰጥተው አብራርተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም፥ ፕሪሜር ዳልተን ማክጊንቲ ስለ መንግሥታቸው ለመላው ኦንታሪያዊያን እያበረከተ ያለውን አገልግሎት ዋና ዋና የፖሊሲና የአፈጻጸም ፕሮግራሞችንበመጥቀስ በሰፊው አስረድተዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኢኮኖሚ ድቀት ካናዳንም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የጣላት መሆኑን የጠቀሱት መሪ፥ ይህ የአሁኑ ትውልድ ካሁን ቀደም አባቶቹና እናቶቹ መስዋእትነት ከፍለው ባስተላ- ለፉለት የሚኮራውን ያህል ያጋጠመውን አስቸጋሪ ጊዜ ተወጠ ለተተኪው ትውልድ መኩሪያና መመኪያ የሚሆን ታሪክ መሥራት አለበት ብለዋል። ከዚህ አያይዘውም መንግሥታቸው ለኦንታሪያዊያን በማገልገል ላይ ያለውን የጤና ጥበቃ፥ የትምህርትና የሥራ ዕድል በላቀና በዳበረ ሁኔታ እንዲቀጥል ይገፉበታል ብለዋል።

ከሚስተር ማክጊንቲ ገለጻ በሁዋላ የየግል መገናኛ ብዙሃናቸውን ወክለው ከተገኙ የስብሰባው ተሳታፊዎች በዛ ያሉ ጥያቀዎችና አስተያየቶች ቀርበዋል። ትኩረት ከተሰጠባቸው ጥያቀዎችና ሃሳቦች መካከል፥ ከውጭ ሀገሮች በተለያዩ ሙያዎች ሠልጥነው ወደ ካናዳ በሚመጡ አዲስ ኑዋሪዎች ላይ ያለው አስከፊ በሙያቸው ተመጣጣኝ የሆነ ሥራ ያለማግኘት አባዜ፥ በውይይት ላይ ያለው ሃርሞናይዝ ታክስ በማህበራዊው የብዙሃን መገናኛዎች ላይ ሊጭን ስለሚችለው ሸክም፥ ስለ ሥራ መስክ መስፋፋት፥ ለማህበረሰብ የብዙሃን መገናኛዎች መደረግ ስለሚኖርበት ድጋፍ ፥ ወዘተ.. ልዩ ልዩ ሃሳቦችና ጥያቀዎች ተነስተው በበቂ ተብላልተዋል።

## ቶሮንቶ ስኮሽያ ባንክ ዋተር ፎል ማራቶን በኢትዮጵያዊያን የበላይነት ተጠናቀቀ፤ በውድድሩ ሦስት ሪኮርድ ተሠበረ

ከገጽ 1 የዞረ

ከ37 ሰኮንድ ሁለተኛ ስትወጣ፥ እንዲሁም ከበቡሽ ሃይሌ 2 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ከ 47 ሰኮንድ ሦስተኛ በመሆን ውድድሩን አጠናቃለች።

በተመሳሳይ በወንዶች በተካሄደው ውድድር ኬንያዊው ኬንዝ ሙንጋራ 2 ሰዓት 08 ደቂቃ ከ 31 ሰኮንድ አሸናፊ ሲሆን፥ ኢትዮጵያዊያኖቹ ጫላ ለሚ 2 ሰዓት ከ08 ደቂቃ ከ48 ሰኮንድ ሁለተኛ፥ እንዲሁም ጋሻው መለስ በ2 ሰዓት ከ09 ደቂቃ ከ12 ሰኮንድ ሦስተኛ በመውጣት ውድድሩን አጠናቀዋል።

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከውድድሩ በሁዋላ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፥ በውድድሩ ወቅት ንፋስና እምቅ እየር እንዳስቸገራቸው ገልጸው፥ የቶ ሮንቶ ኑዋሪዎች በየመንገዱ ዳር በመቆም ለሰጧቸው የሞራል ድጋፍ አመስግነዋል። የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ፕሬዚዳንት ወ/ት አይዳ አሰፋ በውድድሩ ስፍራ በመገኘት በአትሌቶቹ ውጤት የተሰማትን ደስታ ከመግለጿም በላይ ተወዳዳሪዎቹን አበረታትታለች።

የዱከም ምግብ ቤት ባለቤት አቶ ማይክ ቅዱስ ከገቡበት ጊዜ አንስቶ ላደረጉላቸው መስተንግዶና ትብብር አትሌቶቹ አመስግነዋል።

በውድድሩ አንድ መቶ ለሚጠጉ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶ ች መርጃ የሚሆን 1.8 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መሰብሰቡን አስተባባሪዎቹ አስታውቀዋል።

የዚህ ውድድር ዳይሬክተር አለን ብሩክስ በዕለቱ ሦስት ሪከርዶች መሰበራቸው እንዳስደሰታቸው ተናግረዋል።

በዚህ የውድድር ዕለት ሁለት ሯጮች የቀለበት ሥነ ሥርዓታቸውን ፈጽመዋል።

# ህጻንም እንደ ሸቀጥ?

ከገጽ 19 የዞረ

ሁኔታ በእኛነታችን ቀጣይነት ላይ ጥርጣሬን አጭሮአል።

የእኛ ማንነት ማለትም ኢትዮጵያዊነት በሽያጭ ከሀገር የሚወጡትንም የሚያጠቃልል ይመስለኛል። የግለሰብ ማነነት እና የወል ማንነት የግል በየስማችን የምናመጣው ውክልናውም ጥቅሙም የግል የሆነ ማለትም እንደ ሯጭ ሀኪም መሀንዲስ ጠበብት ብቻ የሚዳመቅልን የግላችን ከነማንጠልጠያው ያለው ሲሆን የወል ማንነታችን ደግሞ ኢትዮጵያዊነታችንነው። ታዲያ እንትና ሮጠና ከአለም አንደኛ ወጣ ቢባል እግር አጥቶ አንድም ቀን መሮጥ አይደልም ተራምዶ የማያውቀው ወገኔ ሰለ የወል ማነነቱ መሬት ላይ እየተንፏቀቀ ሲደሰት ብታዩ አትደንቁ የወል ማንነት ውስጣዊ ስሜትን መቆጣጠር አይቻለውምና በይበልጥ ኢትዮጵያዊ ማንነት ታዲይ በግልባጩ የወል ማንነት ከትቢያ ላይ ወድቆ ወደኋላ ሲቆጠር ከአፍሪካ አንደኛ ከአለምም ሁለተኛ ሲወጣ ታዲያ የግል ማንነት በህሊና ሱናሜ እንደሚናወጥ እንዴት ለመግለጽ ተሳነን? የግል ማንነት ከወል ማንነት ውጭ ከውርደትና ሃፍረት አንገት ከማስደፋት ሌላ ሊመጥነው የሚችል ቃል የለም።

በዚህ የህጻናት ንግድ ዙሪያ የደርድርኩትን ከማጠቃለሌ በፊት ግን የማሰሪያ ትዝብቴን አንድ ሁለት እላለሁ

----የተመራመረ በግል ማንነቱ የኮራ ኢትዮጵያዊ ከእኩያ የባዕዳን ጓደኞቹ ጋር በከፍተኛ ሆቴል እየተመገቡ እያለ ሀገራችን ኢትዮጵያ ህጻናትን በመሸጥ ከአለም አንደኛ ለመውጣት እየመራች መሆኑን የሚያሳይ ዜና ድንገት ብልጭ ቢል ሃፍረቱ የሚሸጠው ልጅ ወይንስ......?

------በዚህ ተሰደን ህይወትን ባሸነፍንበት ሃገር ልጆቻችን ባጋጣሚ በዕድል ካደገና ተሸጦ ከመጣ ኢትዮጵያዊ ጋር ቢገናኙና ኢትዮጵያውያን እንደሸጡት ለልጃችን ቢነግርው ሃፍረቱ ተሸጦ የመጣው ልጅ ወይንስ......? እውን ኢትዮጵያውያን ህጻን ይሸጣሉ ? ጉድ የመዓት ዘመን አዎ በትግራይ ነጻ አውጭ ህጻናት ይሸጣሉ።

ታዲያ እንደቀድሞው ጉድ በቻ አውርቶ ሰሞነኛ መፎከሪያ እንዳይሆን በግል የሚያምርብንን ግን ሰብዓዊ ሩጫችንን መጀመር የግድ ይላል። የዚህ ጽሁፍም አላማ ውድ የጋዜጣው አዘጋጅ በዚህ ዙሪያ ሊወለዱ የሚችሉትን የድል ብስራቶች አምድ በመለገስ ያሰተናግዳል በሚል ዕምነትም ጭምር ነው።

ይህንን በወገን ላይ የተነጣጠር ዝርፊያ እያንዳንዳችን ወገናዊ ተሳትፎ በማድረግ ቢያንስ ቢያንስ አንድ አንድ ህጻን በሀገሩ ላይ ለማሳደግ በቤተስቦቻችን አማካይነት ግንኙነት ባስቸኳይ በማድረግ ቢያንስ የአንድ ከርሳም ደላላ ጉሮሮ መዝጋትና እነሱ "ገበያ" የሚሉተን እዛው ሃገር ውስጥ በማስቀረት ወገናዊ ድርሻችንን መወጣት አሁንም ይህ በግል የሚለውን ጉዳይ በድጋሚ ለማብራራት የአንባቢን ጊዜ ከመሻማት የሚዘል ባይሆንም የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት በሚል ስም እየፈሉ የመጡት በአብላጭው ከሃገር ቤት የህጻናት ንግድ ደላሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ወይንም ከጭካኔያቸው ብዛት የትርፍ ተጠቃሚዎች ለመሆናቸው እንድ አሸን መፍላታቸው ጠቋሚ ነውና ከሁሉም ከሁሉም በግል ዕርዳታውን በቤተሰባችን በኩል ማድረጉ ለቅርብ ክትትልም ሆነ ለመንፈሳችን የተረጋጋ እርፍት ይሰጣልና በግል መጀመሩ አማራጭ የለውም ምናልባትም ይህ የወር የአንድ ህጻን ማሳደጊያ ወጭ በቀን እጅግ ለማያስፍልገን ሁለተኛ ቡና የምናጠፋው ነውና ይህ የፉክክር ፊሽካ በሚቀጥለው ዕትም ተብራርቶ በግል የጀመርነው እንዴት ወደ ጋራ እንደሚውስደን የምንመዝንበት ነውና እስከዛው ድረስ መልካም ውድድር የጋራ አሸናፊዎች ነንና ቸር ይግጠመን

ደነቀው ወገኑ

Newspaper & Magazine Layout & Graphics

For All Stages of Prepress Needs

Phone:
416 – 789 – 9933

E-mail:
fmelani@rogers.com

# ያለቀለት ቤት ይጠብቀናል!

ከገጽ 4 የዞረ

"በዚሁ መንገድ ላይ ትገኝ ወረድ ብሎ ሌላ ቤት ሰርቻለሁ። የቤቱ ስራ ከሞላ ጎደል ተጠናቁዋል። ቤቱን እንዳሳያችሁ አብረን እንሂድ።"

"የእኛ ቤቱን ማየት ፋይዳ የለውም። ኣንኩዋን ቤት ለመግዛት ለመከራየት የማስያዣ ገንዘብ የለንም" አልኩ።

"ይሄንን ቤት ያለብዙ ገንዘብ የግላችሁ ለማድረግ የምትችሉ ይመስለኛል። እናንተና እኔ ስለቤት ያለብንን የጋራ ችግር መፍታት የምንችል ይመስለኛል" በማለት ጉዞውን ቀተለ። ኣእኛም የእንቆቅልሹን መጨረሻ ለማወቅ ተከተልነው።

"የህንጻ ሰራተኞች አድማ ደህና አድርጎ ደቁሶኛል፡ ፡መሰረቱ ብቅ ከማለቱ በፊት ያልሸጥኩት ቤት በስራ ታሪኬ ይህ ብቻ ነው። ከአሁኑ ከቤቱ እቃዎች አንድ ጊዜ ተነቃቅለው ተዘርፈዋል። በጣም በመጥፎ ሁኔታ የጎዳኝ ግን ለቤቱ ባንክ እዳ መክፈል መጀመሩ ነው። የንግድ ስራዬ አነስተኛ በመሆኑ ካፒታል በዚሁ ሁኔታ ታስሮ እንዲቀመጥ አልሻም። የበለጠ ከመክሰሬ በፊት ይሄንን ቤት ወዲያ መጣል አለብኝ"

አፎታችንን በአድናቆት ከፍተን ቤት ሰሪውን ሰው ተከተልነው። "ይሁን እንጅ ቤቱን ለመጣል ዝግጁ ብሆንም ለማንም መንገደኛ አልሰጠውም። የባኩን ክፍያ ሳያቋዋርጥ መቀጠል ለሚችል ታማኝ ዜጋ በአነስተኛ ክፍያ እጥለዋለሁ። ጠንካራ ህግ አክባሪና ሃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ስፈልግ ነበር። እጅግ በጣም ጥሩ የብድር መክፈል ታሪክ ያለው ሰውም ስሻ ነበር። ሂል ያንተ ታሪክ ከላይ የዘረዘርኩዋቸውን መልካም ባህርያት የሚያሙዋላ ነው። ስለዚህ ቤቴን ባነስተኛ ዋጋ የምጥለው ላንተ ለሚስተር ሂል ነው;"

"ይህም ቢሆን በስሜ ባንክ ውስጥ ያለን አንድ መቶ ሃምሳ ዶላር ብቻ ነው" በማለት ለመከላከል ሞከርኩ። የትዳር ጉዋደኛየ ጂን ልጅ ማሳደግ ከባድና ብቸኛ ስራዋ ስለሆነ ሌላ ገቢ የሚያስገኝ፡ተግባር የላትም።

"ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ የባንኩን እዳ መክፈል ከጀመርህ የመጀመሪያው ክፍያ እስከዚህም አይደለም" አለ ቤት ሰሪው። ተያይዘን ወደቤቱ ገባን፡፤ አእዲስ የቀለም ቅብ ሽታ ያውዳል። በቤቱ አጋማሽ ወለል ላይ ወርቃማ ምንጣፍ ተዘርግቱዋል። ከፊሉ የወርቅ ቅብ ሽክላ ለብሱዋል። "የቤት ፍላጎት መግለጪ ካርድህጅ አራት ምኝታ ቤትና ሁለት የመኪና ማቆሚያና አንድ የግቢ ውስጥ መዝናኛ እንዲኖረው ያመለክታል። ይህ ቤት ግን ሶሥት ምኝታ ቤቶችና አንድ የመኪና ማቆሚያ ብቻ አለው። ወደፊት እንዳቀማችሁ የጎደለውን ማሙዋላት ትችላላችሁ?" ሲል ጥያቄ አቀረበልን።

ቀልደኛ ነው። ወደፊት አቅማችሁ እንደፈቀደ ማሙዋላት ትችላላችሁ? ልጆች ይዘን በረንዳ የማደር ስጋት እንዳለብን አላወቀም። ከሁለት ቀናት በሁዋላ አዲሱ ቤታችን ውስጥ ገባን። በመጀመሪያ ለቤት ሰሪው የከፈልነው አስራ ሰባት ዶላር ብቻ ነበር።

በዚያው ሳምንት እኔና ቤት ሰሪው ቀሪውን የቤት ስራ አጠናቀቅን። ጂን በትዳር ዘመናችን ከአምክኖ በተፈታውና ከልብዋ በሚመነጨው ንጹህ ስሜት የመንፈስ ቅዱስ አመራርና ግፊት ስቀልድባትና ሳሾፍባት ነበር። እሱዋ ግን ስለኔ ምሁራዊ ትእቢትና የበላይነት ስሜት አንዴም አንስታብኝ አታውቅም ነበር። ዛሬ የመንፈስ የበላይነቱዋ ተገለጠልኝ። ዛሬ እኔ የደረስኩበትን እምነትን በእግዚእብሄር ላይ ብቻ የመጣል ጸጋ አስቀድማ ተቀብላው ነበር። በህይወታችን እግዚአብሄር በልዩ ልዩ መንገዶች መመሪያ ይሰጠናል። አይኖቻችንን፡ ጆሮዎቻችንን አእምሮአቻችንን ግልጽና ክፍት አድርገን በትእግስት፡ በተስፋና በእምነት ጸጥ ብለን መጠበቅ የእኛ ፋንታ ነው። ለብቻችን ሆነን ለልዩ ልዩ አመራሩና በሚያስፈልገን ጊዜ ያለቀለት ቤት እንዲጠብቀን በማድረጉ እግዚእብሄርን አመሰገነው።

ከዚያ አምስት ዓመታት በሁዋላም አልቆለት ሲጠብቀን በነበረው ቤት ውስጥ እንኖራለን። እያደገ ለሄደው ቤተሰባችን ተጨማሪ ክፍል ሲያስፈልገን አዳዲስ ክፍሎችን ቀጠልን። የአትክልት ስፍራና የመዋኛ ገንዳ ጨመርንበት። ልጆች አድገው እራሳቸውን ስለቻሉ ሁለቱን መኝታ ቤቶች የእኔና የጂን ቢሮ አደረግናቸው።

# ለጸረ-ማርያም ተንባላት የቀረበ ምግታር!)

ከገጽ 5 የዞረ

ነውና አሳዝኑዋቸው፥ ከደጅ ወድቆ ሲኖር ንግሥተ አዜብ ታምሪን የሚባል ነጋዴ ወዳጅ ነበራትና የሰለሞንን ጥበብ እያመጣ ይነግራታል፡፡ ሂጄ ልረዳው ብላ መቶ ሃያ መክሊተ ወርቅ ዝባድ (ተምከራ ዘ ኢትዮጵያ ይለዋል) ሉል፥ በውዲያ የማይገኝ በሀገራችን የሚገኝ ሽቱ፥ ገጸ በረከት ይዛ ሂዳለች፡፡ ስትሄድም በየመንገዱ እያስዘራች ሄዳለች፡፡ ስትመለስ ስንቅ እንዲሆናት ነው፡፡ ከእግሯ እንደ ሚዳቁው ሮቀንድ እንደ አህያ ሰኮናም ቢሉ ያለ ነበረባት፡፡ ብላቴናው አይቶ ገብቶ በዘመንህ የማይመጥ ሮየለም፥ እንዲህ ያለች ሴት መጥታለች አለው፡፡ ግቢ በላት አለው፤ ስትገባ ይህ ገባሬ ታእምራት ዕፅ ከደጅ ወድቆ ይኖራል፥ ብትራመደው ደህና ሆናለች፤ በይነ መዓት አየው፤ ንጉሥ ሳላይ አልነገርኩህምና ጠይቀህ ቅጣኝ አለው፡፡ ጠየቃት፤ እውነት ነበረብኝ፥ ነገር ግን ከደጅን የወደቀ ገባሬ ታእምራት ዕፅ አለ፤ እሱ ፈወሰኝ እንጅ አለችው፡፡ እሱ አንድ ብር፥ እሱዋ አንድ ብር ይሸብበብታል፡፡ ከእሳቸውም በሁዋላ የተነሱ ነገሥታት ሃያ ስምንት ናቸው፤ አንዳንድ ብር ይሸብበብታል፡፡ ወርቁንለይሁድ ሮሰጥተው በእንጨቱ ጌታን ሰቅለውታል፡፡"ሐረገወይን ዘእምህሲሶን ይትገዘም ወበጎለጎታ ይተከል፡፡ ሐረገ ወይን ኮነ መድሃኒትየ ዘእምህበ እግዚአብሄር" እንዲል፡፡ አንድም ሰለሞን አዋጅ ነግሮ ዘመተ፥ ሁሉ ሲረዳው ንሥር ሳይረዳው ቀረ፤ በበቀል የ ንሥሩን ግልገል ከግንቡ አግብቶ ዘጋበት፡፡ ንሥር ግልገሉ እዚያ እንዳለ አውቆ ከገነት ዕኸ ቆርጦ አምጥቶ ከግንቡ ጣለው፤ ግንቡ ተሰነጣጠቀ፥ ልጁን ይዞ ሂደ፤ ይህን ቤቱን ሲሠራ ሠረገላ አድርጎ ሠራው፡፡ በዚህ ምክንያት ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት እየተገለጹ ይታዩታል፡፡ እያሠረ ህንድ ያግዛቸው ነበር፡፡ በዚህ ሰቅለውታል፡፡ አንድም ከመቃብረ አዳም የበቀለ ዕፅ ዘይት፥ ሎጥ በእንባው ያለመለመው ዕፅ ታቦተ ጽዮን የመጣችበት ዕፅ ድንባዝ፥ ጌታ በፍኖተ ቢታንያ የረገማት ዕፀ-በለስ ዘኪዎስ የወጣበት ዕፀ ሰግላ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ እንደምን አድርገው ይሰቅሉታል ቢሉ አቁዋሙ አንድ ነው፤ አግዳሚውን ከዚህ ሁሉ ሰብስበው በብረት ጠርቀው ሰቅለውታል . . . "

በትኛውም የፅላት (ታቦት) ገጻዊ ይዘት ላይ ስዕለ ማርያም የግድ መኖር አለበት፡፡ የትኛውም ታቦት የሌላ ጽላት ቢሆንም እንኩዋ፥ በገጹ ላይ ለእመ ብርሃን የተመደበ ቦታ ይኖረዋል፡፡ ይህንንም በማስመልከት በቅዳሴ ማርያሙዋ የአንድምታ መፅሃፍ ላይ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፡፡
. . . ቶሎሳኮ!

## ለፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ መርጃ የተሰናዳው ቶምቦላ ወጣ

ባለፈው ቅዳሜና እሁድ ኦገስት 22 ና 23 ቀን 2009 ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ በተካሄደው የኢሕአፓ 37ኛው የምስረታ ዓመት በዓል ወቅት ለፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ መርጃ የተሰናዳው ቶምቦላ ወጥቶም የሚከተሉት አሸናፊ ሆነዋል።

- 1ኛ የወጣውና ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተር ያገኘው ቁጥር 003234 ከኦሻኒያ
- 2ኛ የወጣውና እችዲቲ ቴሌቪዥን የሚያገኘው ቁጥር 004488 ከሰሜን አሜሪካ
- 3ኛ የወጣውና አይፖድ የሚያገኘው ቁጥር 004485 ከሰሜን አሜሪካ ሲሆን
- የማስተዛዘኛ ሽልማት ያገኘው 003108 አሁንም ከኦሻኒያ ናቸው። አሸናፊዎቹም በቶምቦላው ያገኙትን በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚደርሳቸው ተገልጧል።




# ለምሳሌ የሚሆን ተግባር!



ምሽቱ የገንዘብ ገቢ ብቻ ሳይሆን በዚህ ፎቶ እንደሚታየው መዝ ናናትንም አትርፏል!!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ቶቅርንቶ ውስጥ ዘመናዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ህንጻ ለመገንባት በዕቅድ ላይ መሆናቸው ይታወቃል:: ይህን ቅዱስ ተግባር ለማከናወንና ከፍጻሜ ለማድረስ ላለፉት ጥቂት ዓመታት በተለያዩ መንገዶች ለህንጻው ማሠሪያ የሚሆን ገንዘብ በማሰባሰብ ላይ ናቸው:: ከዚህም አኳያ የሃይማኖት አባቶች በተገኙበትና ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን በማድረግ የተቻለውን ሁሉ ያህል ምእመናኑ ሲረባረቡ መቆየታቸው ሲታወቅ፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ላቅና መጠቅ ባለ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያኗ አባላትና ደጋፊዎች አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

ከሰሞኑ ከታየው አበረታችና ለምሳሌነት የሚጠቀስ እንቅስቃሴ መካከል አንዱ አማኞች የህንጻውን ሥራ ጥረት ለማቀላጠፍና ከግብ ለማድረስ በግል አነሳሽነት እየወሰዱት ያለው እርምጃ ነው:: ከዚህም አኳያ በቶሮንቶ ኑዋሪ ከሆኑት ኢትዮጵያዊያን መካከል በቀደምትነታቸውና በከተማይቱ ውስጥ በሚደረጉ ልዩ ልዩ የ ንግድና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የማህበረሰቡ አባላት የሚያውቋቸው አቶ ኤፍሬም አምዴ ቤተሰቦቻቸውንና ጓደኞቻቸውን በማስተባበር ገንዘብ ለማሰባሰብ ያደረጉት ዘመቻ ነው::

አቶ ኤፍሬም “ከተባበርን ይቻላል!” በሚል መሪ ቃል ተነሳስተው ቶሮርንቶ ውስጥ የመንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ካቴድራል ህንጻ ለማሰራት በሚደረገው ርብርቦሽ ላይ ለየትና ጎላ ያለ እርምጃ በመውሰድ ባለፈው ቅዳሜ ኦክቶበር 10 ቀን 2009 ዓ.ም ታላቅ የመዝ ናኛና ገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት አድርገው ከ21 ሺህ የካናዲያን ዶላር ያላነሰ ገቢ ሰብስበው አ ስረክበዋል:: በዚህ ድርጊታቸውም መላው የቤተ ክርስቲያኗ ተከታይና ለኢትዮጵያ ቅርስና ባህል መስፋፋት መልካሙን የሚያስቡ ሁሉ ከልብ አ መስግነዋቸዋል::

ምንም እንኳ እስካሁንም ቢሆን ምእመናን በቻሉትና ባመቻቸው መንገድ ሁሉ የገንዘብ ማሰባሰቡን ተግባር ሲገፉበት የቆዩ ቢሆንም፥ አሁን ከታየው ተጨማሪ እንቅስቃሴ የተወሰደው ልምድ ደግሞ ቆርጠው ከተነሱ በግል የሚደረግ ጥረትም የብዙሃኑን የጋራ እርምጃ ሊያቀላጥፈው እንደሚችል ነው:: ስለሆነም ሁሉም በያለበት በግሉና ከቤተሰብ ጓደኛው ጋር እንደዚህ ለመሰለ የተቀደሰ ተግባር ምን ሊያደርግ/ልታደርግ እንደሚቻል ማሰላሰል ከተቻለ መፍተሄ እንደማይጠፋ ውጤቱ አ መላክቷል:: ከልብ ለሚታሰብ ነገር የሚገድ የለምና፥ በእርግጥም ይቻላል፤ የዛሬ ዓመት የህንጻው ሥራ ተጠናቆ አገልግሎ ት በመስጠት ላይ ሆኖ ስንመለከት ዛሬ ለምንሠራውና ላደረግነው ሁሉ እማኝ ስለሚሆነን ደስ ይለናል::




www.westernunioncanada.ca moneytransfer

The Contest commences at 12:00:01 a.m. ET on August 17, 2009 and ends at 11:59:59 p.m. on October 31, 2009. For full contest rules, go to www.eidsurprise.com. Each time you send a Western Union Money Transfer® transaction at any participating Western Union® Agent location in Canada (a “qualifying transaction”) to the following countries: Pakistan, Bangladesh, Lebanon, United Arab Emirates, Egypt, Afghanistan, Saudi Arabia, Jordan, Syria, Sudan, Iraq, Turkey, Algeria, Senegal, Tunisia, Ethiopia, Nigeria, Morocco, Palestine, Kuwait, Qatar, Yemen, Bahrain, or Oman, you receive one (1) automatic entry into the Contest. Entrant is deemed to be the person whose name appears as “Sender” on each transaction. Each preceding week’s unsuccessful entries will qualify for a draw in the next week along with the new entries for that week. No Purchase Necessary. To enter without a transaction, hand-print your complete name, address and telephone number on a piece of paper and mail to: Western Union EID Surprise Contest, P.O. Box 250-ES, Pickering, ON, L1V 2R4. **Weekly Prizes:** There will be a total of ten (10) weekly prizes awarded starting on September 8, 2009 and ending November 10, 2009, with one (1) prize awarded weekly. Each weekly prize consists of one (1) EID SURPRISE VOUCHER redeemable for one (1) Round Trip Air Ticket, economy airfare, from Canada to a major international airport located in (A) the capital city (or closest to it) of one (1) of the following countries: Pakistan, Bangladesh, Lebanon, United Arab Emirates, Egypt, Afghanistan, Saudi Arabia, Jordan, Syria, Sudan, Iraq, Turkey, Algeria, Senegal, Tunisia, Ethiopia, Nigeria, Morocco, Palestine, Kuwait, Qatar, Yemen, Bahrain, or Oman, or (B) Jeddah, Saudi Arabia. Confirmation of flight dates and times will be at the sole discretion of the designated travel agency issuing the air tickets. Western Union is not responsible for arranging dates and times of travel. The air ticket will be from any one of the following four (4) major Canadian International Airports nearest the winner’s home: Pearson International Airport, Toronto, Ontario; Vancouver International Airport – Vancouver, BC; Calgary International Airport, Calgary, Alberta, or Pierre Elliott Trudeau International Airport, Montreal, QC, and returning to the same airport. All other expenses such as ground transportation, accommodation, meals, travel documentation fees, airport fees and taxes, spending money and additional travel beyond the destination mentioned on the Air Ticket will be the sole responsibility of the winner. Approximate retail value of each prize voucher is $2,000.00 Cdn. The winner will have the option of taking a $1,500.00 (Cdn) cash equivalent in lieu of the EID SURPRISE VOUCHER. Odds of winning depend on the number of eligible entries received. In order to win, the selected entrant must first correctly answer a mathematical skill-testing question and sign a Declaration and Release Form. **Québec Residents:** Any litigation respecting the conduct or organization of a publicity contest may be submitted to the Régie des alcools, des courses et des jeux for a ruling.